# የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ

## ትምህርት አራት

# መንፈስ ቅዱስ

ተርጓሚ፡ እሸቴ በለጠ

The Apostles' Creed

Lesson Four

The Holy Spirit

THIRD MILLENNIUM MINISTRIES

Biblical Education. For the World. For Free.

# ማውጫ


## 1. መግቢያ

## 2. መለኮትነት

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ

ውቅር

የኢየሱስ መፀነስ

መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት

ስሞች

የባህርይ መገለጫዎች

ሥራ

ቀመሮች

## 3. ስብዕና

የባህርይ መገለጫዎች

መለያ

ተዛምዶ

## 4. ሥራ

የመፍጠር ኃይል

ፍጥረታዊ ዓለም

መንፈሳዊ ስጦታዎች

ግለሰባዊ ኅዳሴ

ቅድስና

ጸጋ

የወል ጸጋ

ቃል ኪዳናዊ ጸጋ

የድነት ጸጋ

መገለጥ

አጠቃላይ መገለጥ

ልዩ መገለጥ

አብርሆት እና ውስጣዊ ምሪት

## 5. መደምደሚያ

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. In 2009 ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡፡

# 1. መግቢያ

ማንኛውም ክርስቲያናዊ ባህል የራሱ አጽንዖት አለው፡፡ አንዳንድ ልማዶች በአምልኮ ላይ አጽንዖት ይሰጣሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ በአስተምህሮና በእውነት ላይ አፅንዖት ያደርጋሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ በማኅበራዊ ተሳትፎና ሥራ ላይ አፅንዖት ያደርጋሉ፡፡ ጥቂቶቹ ደግሞ በአማኞች አንድነት ላይ ያተኩራሉ፡፡ ጥቂቶቹ በተነቃቃ የክርስትና አኗኗር ላይ ያተኩራሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ መልካም አፅንዖቶች ናቸው፡፡

ሆኖም በአብዛኞቹ ክርስቲያኖች ቸል የተባለ ግን የሁላችንንም ትኩረቶች የሚያስተሳስር ሊሰመርበት የሚገባ አንድ እውነታ አለ፡፡ እርሱም በክርስቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ መልካም ነገሮች ሁሉ የሚፈልቁበት እርሱ ነው፡፡ እርሱም በእነዚህና በሌሎችም በክርስቲያናዊ እምነት ነገረ ጉዳዮች ላይ ኃይልን የሚያስታጥቀንና የሚያበረታታን ስብዕና ነው፡፡ እርሱ ዘወትር ከእኛ ጋር ነው፣ ድነትንም በሕይወታችን እውን ለማድረግ ያቃትታል፡፡ እርሱ በውስጣችን የሚኖር ሕይወታችን ነው፡፡ እርሱም ሌላ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡

በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ላይ ከምንማረው ተከታታይ ትምህርት አራተኛው ትምህርታችን ነው፡፡ ይህንንም ትምህርት “መንፈስ ቅዱስ” የሚል ርዕስ ሰጥተነዋል ምክንያቱም የምናተኩረው በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው ላይ በተቀመጠውና የአሃዱ-ስሉስ አምላካችን አካል በሆነው በመንፈስ ቅዱስ ላይ ያለንን እምነት በሚያጸናው አንቀጽ ላይ ስለምናተኩር ነው፡፡

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው የመንፈስ ቅዱስን ርዕሰ ጉዳይ በቀጥታ የሚያነሳው በአንድ ነጠላ መስመር ነው፡

*በመንፈስ ቅዱስ አምናለሁ፡፡*

በሃይማኖት መግለጫው ስለ መንፈስ ቅዱስ የተገለጠበት ሌላ ዐረፍት ነገር ኢየሱስ በማርያም ማኅፀን እንዲፀነስ ማድረጉ ነው፡፡ እንደምትመለከቱት የሃይማኖት መግለጫው ስለ መንፈስ ቅዱስ የተናገረው በጣም በጥቂቱ ነው፡፡ ሆኖም በታሪክ ዘመናት ሁሉ ለነበሩ ክርስቲያኖች ወሳኝ የሆኑ ጠቃሚ እውነታዎችን አመልክቷል፡፡

ስለ መንፈስ ቅዱስ የምናደርገው ውይይት በሦስት ክፍሎች የተከፈለ ነው፡፡ በመጀመሪያ፣ ስለ መለኮትነቱ እንነጋገራለን፣ ያም ሙሉ በሙሉ የስላሴ አካል መሆኑን ማለት ነው፡፡ ሁለተኛ፣ ስብዕናውን እንመለከታለን፣ መንፈስ ቅዱስ እውነተኛ ስብዕና ያለው እንጂ እንዲያው መለኮታዊ ኃይል ብቻ አይደለም፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ባለፉት ዘመናት የሠራቸውን

እና ዛሬም እየሠራቸው ያሉ ሥራዎቹን እንመረምራለን፡፡ በመንፈስ ቅዱስ መለኮትነት እንጀምር፡፡

# 2. መለኮትነት

የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት ለመቃኘት፣ በሁለት አቅጣጫዎች እንመለከተዋለን፡፡ በአንድ በኩል፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ የመንፈስን መለኮትነት ማረጋገጡን እንመለከታለን፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ስለ ሃይማኖት መግለጫው አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቶችን እንመለከታለን፡፡ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት ያረጋገጠበትን መንገድ በመመልከት እንጀምር፡፡

## የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ

*ስለ መንፈስ ቅዱስ ስብዕና ስለመነጋገር ስናነሳ፣ ሰዎች በተደጋጋሚ የሚያነሱት ጥያቄ ቤተክርስቲያን ዘወትር የመንፈስ ቅዱስን መለኮትንት ማረጋገጥ ወይንም ማወጅ ይገባታል ወይስ አይገባትም የሚለውን ነው፡፡ እናም በእርግጠኝነት የኒቂያው የሃይማኖት መግለጫ እና የኒቂያው ጉባኤ ሙሉ በሙሉ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስብዕና ግልፅ አላደረገም፣ ስለዚህም ሌላ ጉባኤ ተካሂዶ ነበር፣ ያም የኬልቄዶኑ ጉባኤ እንደነበር አምናለሁ፣ የኬልቄዶኑ ጉባኤ መንፈስ ቅዱስ ልክ እንደ ወልድ ሁሉ ሙሉ በሙሉ ሊመለክ የሚገባው መለኮት መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ስለዚህም አንዳንድ ሰዎች "ቤተክርስቲያን ዘወትር የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት ማወጅ አይገባትም" እንዲሉ ምክንያት ሆኗቸዋል፡፡ እኔ እንደማስበው ግን ይህ ስህተት ነው፡፡ ጉባኤዎቹ አዲስ አስተምህሮ ለማውጣት በፍፁም አልተጠሩም፡፡ ጉባኤዎቹ ዘወትር የሚጠሩት የቤተክርስቲያንን ታሪካዊና ትውፊታዊ አስተምህሮ አስመልክቶ ያለውን መረዳት በስህተት እንቅስቃሴዎች ፊት ለማብራራት ነው፡፡ ስለዚህም ጉባኤዎቹ ባወጡት መግለጫ ምክንያት፣ ከሐዋርያት ዘመን አንስቶ፣ እና ሐዋርያዊ አባቶችና ቀደምት የቤተክርስቲያን የነገረ- መለኮት ሊቃውንት ያወጁትን ስንመረምር፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ መለኮትነት ያሉ አስተምህሮዎችን እናገኛለን፡፡ [ዶ/ር ስቲቭ ብላክሞር]*

ከውጪው ስንመለከተው፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው መንፈስ ቅዱስ መለኮት ነው ብሎ ነጥሎ ያላስቀመጠ መሆኑን ልንቀበል ይገባል፡፡ ግን ቢያንስ በሁለት መንገዶች ስለ መንፈስ ቅዱስ መለኮትነት በውስጡ ማረጋገጫ እንደሰጠ እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የስላሴ አወቃቀሩ ለመንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ እኩል ስፍራ ይሰጠዋል፡፡ ሁለተኛ፣ ስለ ኢየሱስ መፀነስ የሃይማኖት መግለጫው የሰጠው መግለጫ መንፈስ ቅዱስ መለኮት መሆኑን

ያመለክታል፡፡ የሃይማኖት መግለጫውን የራሱን አወቃቀር በመመልከት ሁለቱንም ጉዳዮች እንመልከታቸው፡፡

# ውቅር

ቀደም ባለው ትምህርታችን፣ የሃይማት መግለጫውን ከትምህርተ እግዚአብሔር አንፃር ስንቃኘው፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ሦስት ዋና ክፍሎች ያሉትና፣ እያንዳንዳቸውም "አምናለሁ" በሚል ቃል እንደሚደመደሙ ተመልክተናል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል ስለ እግዚአብሔር አብ ያለን አመለካከት ያነሳል፡፡ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ስለ አንድያ ልጁ፣ ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ያለን እምነት ያነሳል፡፡ ሦስተኛው ክፍል ደግሞ ስለ መንፈስ ቅዱስ ያለን እምነት ጠቅለል አድርጎ ያነሳል አገልግሎቶቹንም ይጠቅሳል፡፡

ቀደም ባለው ትምህርት፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው በጊዜ ብዛት እንዳደገ እንደመጣና ቀደምት ቅጂዎቹ በአጥቢያ የጥምቀት ስርዓት የሚነገሩ የእምነት መግለጫዎች እንደ ነበሩ ተመልክተናል፡፡ ከነዚህ ጥንታዊ የሃይማኖት መግለጫዎች አንዳንዶቹ ስለ ኢየሱስ ከሚናገረው አረፍተ ነገር መደምደሚያ ላይ "አምናለሁ" የሚለውን አስገብተዋል፡፡ ሌሎቹ ግን በ700 ዓ.ም. እንደ ወጣው ድንጋጌ አይነት በቀላሉ "እና" የሚለውን ብቻ ይጠቀማሉ፡፡ የቃላት አጠቃቀማቸውን ብንተወው ሃሳቡ ግን ተመሳሳይ ነው ማለትም የሃይማኖት መግለጫው የተከፈለው በሦስቱ የእግዚአብሔር ስብዕና አንፃር ነው፡፡ ይህም ክፍፍል በዓለም አቀፍ ደረጃ በቤተክርስቲያን እውቅና የተሰጠው ነው፡፡ ይህ የስላሴ ቀመር አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ተብለው በሚጠሩ ሦስት ስብዕናዎች የተገለጠ አንድ አምላክ የሚለውን እምነት ይገልጣል፡፡

ከ170 እስከ 236 ዓ.ም. የኖረው ቀደምት የቤተክርስቲያን አባት ሒፖሊተስ፣ በእርሱ ዘመን አገልግሎት ላይ ይውል የነበረው የጥምቀት የሃይማኖት መግለጫ የስላሴን አወቃቅር በግልጥ ያስቀምጥ እንደነበረ አብራርቷል፡፡ የእምነት መግለጫው የጀመረው በአጥቢያ ደረጃ ነው፣ በኋላ ግን በውል በሚታይ መንገድ እያደገ ተስፋፍቷል፡፡ ቋንቋውም ከዘመናዊው የሃይማኖት መግለጫ ጋር በጣም ይመሳሰላል፣ በጥምቀት ሥርዓቶች የሚነገርበት መንገድ ግን ስላሴያዊ አፅንኦቱ ጠንከር ይላል፡፡

ሒፖሊተስ ጥምቀት የሚካሄደው ሰውየውን ሦስት ጊዜ በውሃ ውስጥ በማጥለቅ እንደሆነ ያብራራል፡፡ በእያንዳንዳቸው መጥለቆች ወቅት፣ የሚጠመቀው ሰው በየክፍሎቹ የሚነሳውን የስላሴ አካል በማስረገጥ ያውጃል፡፡ አስቀድሞ ሰውየው በሃይማኖት መግለጫው ስለ አብ ያለውን የእምነት አንቀፅ ያውጃል፤ ከዚያም ይጠልቃል፡፡ ቀጥሎ ደግሞ ስለ ወልድ በሃይማኖት መግለጫው የተጠቀሰው የእምነት አንቀፅ ይከተላል፤ ሁለተኛውም መጥለቅ ይፈጸማል፡፡

በመጨረሻም ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተገናኙት አንቀፆች ይከተላሉ፤ ሦስተኛውና የመጨረሻውም መጥለቅ ይከናወናል፡፡ በነዚህና በሌሎችም በቀደምት ቤተክርስቲያን በሚደረጉ ልምምዶች፣ የሃይማኖት መግለጫው አወቃቀር በራሱ የስላሴን እያንዳንዱን ስብዕና መለኮትነትና ሥራ፣ መንፈስ ቅዱስን ጨምሮ አፅንኦት ለመስጠት በዓላማ የተቀረፀ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት ያረጋገጠበት ሁለተኛው መንገድ በኢየሱስ መፀነስ ወቅት የሆነውን በማብራራት ነው፡፡

# የኢየሱስ መፀነስ

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ፣

*በመንፈስ ቅዱስ የተፀነሰ*

ነው ይለናል፡፡

ይህ አረፍተ ነገር መንፈስ ቅዱስ ምሉዕ መለኮት ነው ብሎ ነጥሎ አይነግረንም፣ ይህንን እምነትን ግን ያመላክተናል፡፡ ስለ ኢየሱስ መፀነስ ስንነጋገር፣ የሃይማኖት መግለጫው በሉቃስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 35 መልአኩ ለማርያም እንዲህ ሲል ከተናገራት ጋር ይስማማል፡-

> መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፡- መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፥ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል። (ሉቃስ 1፥35)

በዚህ ጥቅስ፣ መንፈስ ቅዱስ ከልዑሉ ኃይል ጋር በአቻ ተቀምጧል፡፡ በዚህ ትምህርት ወደ ኋላ እንደምንመለከተው፣ እግዚአብሔር ብቻ ነው ከፍ ያለው ልዑል ኃይል ያለው፡፡ ስለዚህም የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ከዚህ ጥቅስ ጋር በማዛመድ፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው የመንፈስ ቅዱስን ምሉዕ መለኮትነት ያረጋግጥልናል፡፡ ይህም ድምዳሜ በዕብራውያን ምዕራፍ 10 ከቁጥር 5 እስከ 7 እንዲህ በሚነበበው ተረጋግጧል፡

> ስለዚህ ወደ ዓለም ሲገባ። መሥዋዕትንና መባን አልወደድህም ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ፤
> በሙሉ በሚቃጠል መሥዋዕትና ስለ ኃጢአት በሚሰዋ መሥዋዕት ደስ አላለህም።
> በዚያን ጊዜ። እነሆ፥ በመጽሐፍ ጥቅልል ስለ እኔ እንደ ተጻፈ፥ አምላኬ

*ሆይ፥ ፈቃድህን ላደርግ መጥቼአለሁ አልሁ (ዕብ 10፥5-7)*

በዚህ ስፍራ፣ የኢየሱስን ሰብዓዊ ሰውነት የመፍጠሩ ሥራ የእግዚአብሔር ብቻ መሆኑ ተነግሮናል፡፡ ይህንን በመሳሰሉት ጥቅሶች ብርሃን መሠረት፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው የኢየሱስን መፀነስ ከመንፈስ ቅዱስ ሥራ ጋር ሲያገናኘው፣ የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት ማረጋገጥን ዓልሞ መሆኑን መናገር ተገቢ ነው፡፡

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት እንዴት እንደገለጠው ከተመለከትን፣ ስለ ሚናገረው ነገር ያሉትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቶች እንመልከት፡፡

# መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት

ዛሬ እኛ የምናረጋግጠው የእምነት አቋም ለበርካታ ምዕተ-ዓመታት ያለማቋረጥ ሲረጋገጥ የቆየ መሆኑን እውቅና መስጠት ትልቅ ዋጋ አለው፡፡ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ስለ መንፈስ ቅዱስ መለኮትነት የሚያስተምረውን መረዳት ያስፈለገበትም አንዱ ምክንያት ይኸው ነው፡፡ ምንም እንኳን መተማመኛችን የተወሰደው ከቅዱሳት መጻሕፍት ቢሆንም እንኳን ማለት ነው፡፡ ለሃይማኖት መግለጫው የምንሰጠው ዋጋ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንደሚተካ ሳይሆን፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ጠቅለል አድርጎ የሚያቀርብልን እንደሆነ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ዘወትር የሃይማኖት መግለጫው የሚናገረው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡

*ቅዱሳት መጻሕፍት የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት ቢያንስ በአራት መረዳቶች እንደሚያረጋግጡልን መመልከት እንችላለን፡፡ አንደኛ፣ በአንዳንድ ምንባቦች መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ጋር በተለዋዋጭነት የመቅረቡ እውነታ መገለጡ፡፡ ሁለተኛው የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት ማስረጃ ለእግዚአብሔር ብቻ የሚሰጡ የባህርይ መገለጫዎች ለመንፈስ ቅዱስም መሰጠታቸው ነው፡፡ ሦስተኛ፣ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ብቻ ሊሠራ የሚችለውን ሥራ መሥራቱ ነው፡፡ በማቴዎስ 28 ክርስቲያኖች በማን ስም እንደሚጠመቁ ሲገለጥ መንፈስ ቅዱስም በነጠላ ስም መጠቀሱ የመጨረሻው ነው፡፡ [ዶ/ር ኬት ጆንሰን]*

የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት እንድናምን የሚያስችለን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የተገለጠው በብዙ መንገዶች ነው፡፡ ለአሁኑ ዓላማችን ግን፣ በተጠራባቸው ስሞቹ፣ ባሉት የባህርይ መገለጫዎች፣ በሠራቸው ሥራዎች እና ከእርሱ ጋር በተጣቀሱ የስላሴ ቀመሮች ላይ እናተኩራለን፡፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ለመንፈስ ቅዱስ ከተሰጡት ስሞች እንጀምር፡፡

# ስሞች

በመጽሐፍ ቅዱሳችን መንፈስ ቅዱስ በበርካታ ስሞች ተጠርቷል፡፡ ከነዚህም ስሞች ጥቂቶቹ በጣም ስውር በሆነ መንገድ መለኮትነቱን ይነግሩናል፡፡ ሌሎቹ ደግሞ በግልጽ መለኮት ብለው ይጠሩታል፡፡ ሌሎችም ደግሞ በሁለቱም መካከል የሚቆሙ አሉ፡፡

ስውር በሆነ መንገድ የእርሱን መለኮትነት የሚገልጠው ስም "መንፈስ ቅዱስ" የሚለው ስም ነው፡፡ "ቅዱስ" የሚለው ቃል መለኮትነት ለሌላቸው ፍጡራንም በሆነ መንገድ አገልግሎት ላይ ይውላል፡፡ "ቅዱስ" የሚለው ቃል በጥቅሉ የሚያመለክተው በአንድ መንገድ ለእግዚአብሔር በመለየታቸው ምክንያት ከመሰሎቻው ለየት የሚሉ ነገሮችን ነው፡፡ እንግዲያው "ቅዱስ" የሚለው ቃል በራሱ የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት አያመለክትም፡፡

ሆኖም፣ በብሉይ ኪዳን ከዳር እስከ ዳር፣ "ቅዱሱ" ተብሎ በተደጋጋሚ የተጠቀሰው፣ እግዚአብሔር መሆኑን ማስታወስ ግን ይገባል፡፡ ይህንንም በበርካታ ምንባቦች ማግኘት ይቻላል፣ ለአብነትም፣ 2ኛ ነገሥት ምዕራፍ 19 ቁጥር 22፣ ኢሳያስ ምዕራፍ 30 ቁጥር 11 እስከ 15 እና ሆሴዕ ምዕራፍ 11 ከቁጥር 9 እስከ 12፡፡ እግዚአብሔርን ራሱን መንፈስ ቅዱስ የሚል ስም የሰጡ የሚመስሉ ሌሎች ምንባቦችንም እናገኛለን፣ ለምሳሌ፣ ኢሳያስ ምዕራፍ 63 ቁጥር 10 እና 11፡፡ ይህንን መሳዩን መጠሪያ በጥንታዊው ግን የመንፈስ ቅዱስ መነዳት በሌለበት የጥበብ መጽሐፍ በሚባለው የአይሁድ ስነ-ጽሁፍ ምዕራፍ 9 ቁጥር 17 ላይም እናገኘዋለን፡፡ ይህንን የብሉይ ኪዳን ጠብታ በማንሳት፣ "መንፈስ ቅዱስ" በሚለው ስም ውስጥ የመለኮትነት እንድምታ እንዳለ መመልከት አግባብነት አለው፡፡

እነዚህን በጣም ስውር ስሞች በአዕምሯችን እንያዝና፣ በጣም ግልጽ እና በጣም ስውር በሆኑት መካከል ሆነው የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት የሚያመለክቱ ስሞችን እንመልከት፡፡ እነዚህም ስሞች "የጌታ መንፈስ"፣ "የእግዚአብሔር መንፈስ"፣ "የሕያው እግዚአብሔር መንፈስ" የሚሉ ናቸው፡፡ በተጨማሪም፣ "የኢየሱስ መንፈስ"፣ "የክርስቶስ መንፈስ"፣ "የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ" የሚሉ ናቸው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ፣ "የአባትህ መንፈስ"፣ "የልጁ መንፈስ"፣ "ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው የእርሱ መንፈስ" የሚሉ ናቸው፡፡ እነዚህም ስሞች ልክ ሰው ከራሱ መንፈስ ጋር አንድ እንደ ሆነ ሁሉ እግዚአብሔርም ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ እንደሆነ በማመልከት መንፈስ ቅዱስ መለኮት ነው ብለው ይናገራሉ፡፡ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 11 እነዚህን ቃላት ሲጽፍ በግልፅ ይህንን ግንኙነት አመልክቷል፡፡

በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም። (1ቆሮ 2፥11)

የእኛ መንፈሶች የእኛ ሰብዓዊነት ክፍሎች ናቸው፡፡ ምንም ከሰብዓዊነት የሚጎድሉበት ነጥብ የለም፡፡ ምሉዕ ሰብዓዊ ናቸው፡፡ በተመሳሳይም መንገድ መንፈስ ቅዱስም ምሉዕ መለኮት ነው፡፡ የአብን ልብ እንዲያውቅ ያስቻለውም ይኸው ነው፡፡ ስለዚህም፣ ለክርስቲያኖች የአብን ልብ በመግለጥ ስራው፣ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር መሆኑን ገልጧል፡፡

በመጨረሻም፣ መንፈስ ቅዱስን በግልጥ "እግዚአብሔር" የሚል ስም የሰጡ ምንባቦችም አሉ፡፡ ጴጥሮስ ለሐናንያ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 5 ከቁጥር 3 እስከ 4 የተናገረውን አድምጡ

ጴጥሮስም፡- ሐናንያ ሆይ፥ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ
ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለ ምን ሞላ?
ሳትሸጠው የአንተ አልነበረምን? ከሸጥኸውስ በኋላ በሥልጣንህ
አልነበረምን? ይህን ነገር ስለ ምን በልብህ አሰብህ? እግዚአብሔርን እንጂ
ሰውን አልዋሸህም አለው። (ሐሥ 5፥3-4)

በዚህ ምንባብ፣ ጴጥሮስ በመጀመሪያ የተናገረው ሐናንያ መንፈስ ቅዱስን እንደዋሸ ነበር፡፡ በኋላ ጴጥሮስ ምን ማለቱ እንደሆነ ሲያብራራ ሐናንያ እግዚአብሔርን እንደዋሸ ተናገረ፡፡ በዚህ ስፍራ ሐዋርያው ጴጥሮስ በግልፅ መንፈስ ቅዱስን "እግዚአብሔር" ብሎ ጠራው፡፡

እንግዲያው፣ መንፈስ ቅዱስ በቅዱሳት መጻሕፍት የተጠራባቸውን ስሞች ስንመለከት፣ መለኮትነቱን በጣም ስውር በሆነ መንገድ ከመግለጥ አንስቶ በጣም በግልጥ እስከማንሳት እንደሚዘልቁ አይተናል ማለት ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት የገለጠበት ሁለተኛ መንገድ መለኮታዊ የባህርይ መገለጫዎችን ለእርሱ በመስጠት ነው፡፡

# የባህርይ መገለጫዎች

የክርስቲያን ነገረ መለኮት ምሁራን በትውፊት እንደሚናገሩት እግዚአብሔር ሁለት የተለዩ የባህርይ መገለጫዎች አሉት ይላሉ፡ የሚተላለፉ እና የማይተላለፉ የባህርይ መገለጫዎች ናቸው፡፡ በአንድ በኩል፣ ወደ ፍጥረቶቹ በቀላሉ "የተላለፉ" ወይም "የሚጋሩ" ተላላፊ የባህርይ መገለጫዎች አሉት፡፡

ለአብነት ያህል፣ እግዚአብሔር ከሰብዓዊ ፍጡራት ጋር የሚጋራው አመክንዮአዊ ባህርይ አለው፡፡ ወስን ፍጡራን እንደመሆናቸው መጠን፣ የሰው ልጆች የእግዚአብሔርን አመክንዮ ሙሉ በሙሉ ሊገልጡ አይችሉም፡፡ ሆኖም ግን ምክንያታዊ በሆነ መንገድ የማሰብ አቅም አለን፡፡ ይህ ማለት ግን መለኮት ነን ማለት አይደለም፡፡ በቀላሉ የሚያረጋግጥልን የእርሱን አመክንዮአዊ ባህርይ በተወሰነ መጠን ለእኛ ባስተላለፈ አስተዋይ በሆነ አምላክ የተፈጠርን መሆኑን ነው፡፡ የእኛ ምክኑያዊነት የተገኘው ከእርሱ ነው፤ እኛ ፍጥረቱ በመሆናችን ምክንያት የእርሱን አመክንዮአዊ ባህርይ እናንፀባርቃለን፡፡

ሌላኛው የእግዚአብሔር የሚተላለፍ ባህርይ ፍቅሩ ነው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍትም በበርካታ ቦታዎች ለሰዎች ያለን ፍቅር፣ ለእግዚአብሔርም ያለን ፍቅር፣ በቀጥታ የተቀዳው ከእግዚአብሔር የፍቅር ባህርይ ነው፡፡ ይህንንም እንደ ገላትያ ምዕራፍ 5 ቁጥር 2፤ ኤፌሶን ምዕራፍ 5 ቁር 1፤ 2ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 7 እና 1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 4 ከቁጥር 7 እስከ 21 ባሉት ክፍሎች እናገኘዋለን፡፡

እግዚአብሔር ግን የማይተላለፉ ባህርያትም አሉት፣ እነርሱም በማንነታቸው ወደ ፍጥረቱ በፍፁም የማይተላለፉ ባህርያት ናቸው፡፡ በጣም ከሚታወቁ የማይተላለፉ የእግዚአብሔር ባህርያት መካከል ሁሉን አዋቂነቱ፣ ማለትም የእርሱ የማይገደብ እውቀቱ፣ መረዳቱና ጥበቡ፤ ሁሉን ቻይነቱ፣ ይህም የማይገደበው ኃይሉ፤ በሁሉ ስፍራ በአንድ ጊዜ መገኘቱ እና ዘላለማዊነቱ፣ ይህም የማይገደበው እና የማይቋረጠው በማንም የማይደገፍ ኑባሬው ናቸው፡፡ እነዚህ የእግዚአብሔር የማይተላለፉ ባህርያት የእርሱ የብቻው በመሆናቸው ምክንያት፣ ከእነዚህ አንዱን ወይንም ከዚያም በላይ ይዞ የተገኘ መሆኑን በማሳየት መንፈስ ቅዱስ አምላክ መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን ስንዳስስ ያንን እናገኛለን፣ እንዲያውም፣ ሁሉንም ይዞ እናገኘዋለን፡፡ አስቀድመን የመንፈስ ቅዱስን ሁሉን አዋቂነት እንመልከት፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍት መንፈስ የእግዚአብሔርን ልብ ያውቃል ይላሉ፡፡ ይህንንም በኤፌሶን ምዕራፍ 1 ቁጥር 17 እና በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 10 እና 11 ውስጥ እናገኛለን፡፡ በመሠረቱ፣ የእግዚአብሔር ልቡና የማይገደብ ነው፣ ስለዚህም በትክክል ለመረዳት እኩያ የማይገደብ ማንነት ያስፈልጋል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ሁሉን አዋቂውን የእግዚአብሔርን ልቡና ለመረዳት በመቻሉ፣ መንፈስ ቅዱስ ራሱ የማይገደብ መሆኑ ይረጋገጣል፡፡ ሁሉን አዋቂ በመሆኑም አምላክ ሊሆን ግድ ነው፡፡

መንፈስ ቅዱስ አምላክ መሆኑ በሁሉን ቻይነቱም ተረጋግጧል፡፡ የእርሱ ኃይል የማይገደበው የእግዚአብሔር ኃይል ነው፡፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ በርካታ ምንባቦች ስለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል ይናገራሉ፣ ለምሳሌም፣ 1ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 10 ቁጥር 6፤ ሮሜ ምዕራፍ 15ቁጥር 19፤ 1ኛቆሮንቶስ ምዕራፍ 12 ቁጥር 11 እና 1ኛተሰሎንቄ ምዕራፍ 1 ቁጥር 5፡፡ መንፈስ

ቅዱስ ከእግዚአብሔር ኃይል ጋር ያለውን ግንኙነት በዘፍጥረት ምእራፍ 1 ከቁጥር 1 እስከ 3 ላይ እንመልከት፡

> በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ። ምድርም ባዶ ነበረች፥ አንዳችም አልነበረባትም ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር።
>
> እግዚአብሔርም፡- ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ። (ዘፍ 1፥1-3)

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፣ በብሉይ ኪዳን ስለ እግዚአብሔር የተሰጡ ማጣቀሻዎች በጠቅላላ ስለ ስላሴ ነው የሚያመለክቱት፡፡ ሆኖም ቋንቋውን ወይም አውዱን መሠረት በማድረግ፣ በአንዱ ወይንም በሌላው ማንነት ላይ ያለውን አፅንኦት መመልከቱ አግባብነት አለው፡፡ በያዝነውም ርዕሰ ጉዳይ፣ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስ በመሆኑ ሰብዕና ላይ እናተኩራለን፡፡ ስለዚህም፣ ብርሃንን የመፍጠሩ ሥራ የመንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ በሌሎቹም እግዚአብሔር በዚህ ምዕራፍ በፈጠራቸው ፍጥረታትም ነገሩ እንደዚያው ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ይህንን መሳዩን ሁሉን ቻይነት ይዞ ይገኝ ዘንድ፣ ካልነበረ ነገር ውስጥ አንድን ነገር ለመፍጠርም፣ ምሉዕ መለኮት ሊሆን ይገባዋል፡፡

ሌላኛው የማይተላለፍ የመንፈስ ቅዱስ ባህርይ በሁሉ ስፍራ በአንድ ጊዜ መገኘቱ ነው፡፡ መዝሙር 139 ቁጥር 7 እስከ 10 ያለው ምንባብ ከባህሩ ጥልቅ እስከ መንግሥተ ሰማያት ከፍታ ድረስ መንፈስ ቅዱስ በፍጥረተ ዓለሙ ክፍሎች ሁሉ በአንድ ጊዜ እንደሚገኝ ያስተምረናል፡፡

መንፈስ ቅዱስ የዘላለማዊነት ባህርይ አለው፡፡ ዕብራውያን ምዕራፍ 9 ቁጥር 14 መንፈስ ቅዱስን "የዘላለም መንፈስ" በማለት ይገልጠዋል፡፡ ማለትም እርሱ ለዘላለም አለ፣ ለዘላለምም ይኖራል፡፡

በእነዚህ የማይተላለፉ የባህርይ መገለጫዎች እና እነርሱን በሚመስሉ በሌሎችም፣ መንፈስ ቅዱስ አምላክ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በግልፅ ያመለክታል፡፡

# ሥራ

ስለ ክርስቶስ መለኮትነት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የምናገኘው ሦስተኛ ማስረጃ እርሱ የሠራው ሥራ ዓይነት ነው፡፡ በዚህ ትምህርት ወደ ኋላ ላይ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በበለጠ ጥልቀት እንመለከታለን፡፡ ለአሁኑ ግን፣ የእርሱን መለኮትነት እንዴት አድርገው እንዳመለከቱ በፍጥነት ዳሰስ እናደርጋለን፡፡

*ለዚያም ማረጋገጫ ከቅዱሳት መጻሕፍት የምናገኝበት አንዱ መንገድ ሥራውን መመልከት ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ስለ ክርስቶስ የሚመሰክር፣ እኛን ከክርስቶስ ጋር የሚያገናኝ፣ አዲስን ሕይወት የሚሰጥ፣ ትንሣኤን የሚያስገኝ፣ በመፍጠር ሥራ የተካፈለ ነው፡፡ እነዚህ ሥራዎች የእግዚአብሔር ሥራ ከመሆን ያነሱ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ለሰዎች ተግባራዊ ሊሆኑ አይችሉም፤ ለመላእክት ሠራዊቶች ወይንም ለሌሎች ፍጡራን ተግባራዊ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ እነርሱ እግዚአብሔር ብቻ ሊያከናውናቸው የሚችላቸው ናቸው፡፡ በዚያም መሠረት፣ መንፈስ ቅዱስ የሚሠራው እግዚአብሔር የሚሠራውን ነው፣ እናም ያ ሰብዓዊ ብቻ ሳይሆን መለኮታዊም ነው ማለት ነው፡፡*

መጽሐፍ ቅዱስ ለእግዚአብሔር ብቻ አግባብነት እንዳላቸው እና መለኮታዊ ኃይልና የባህርይ መገለጫ እንዳለባቸው የሚያመለክታቸውን በርካታ ሥራዎች መንፈስ ቅዱስ ይሠራል፡፡ ለምሳሌ፣ ሮሜ ምዕራፍ 8 ቁጥር 11 ስናነብብ፣ መንፈሳችንን እንደገና ሲያድስ አዲስ ሕይወት ይፈጥራል፡፡ ከሮሜ ምዕራፍ 5 እስከ 8 እንደምንማረው ድነትን በሕይወታችን ይተገብራል፡፡ ሮሜ ምዕራፍ 15 ከቁጥር 4 እስከ 19 በመሳሰሉት ምንባቦች እንደምናነብበው፣ ከነቢያት የተዓምራት አገልግሎት፣ እንዲያውም ከኢየሱስም ከራሱ አገልግሎት በስተጀርባ ያለው ኃይል የእርሱ ነው፡፡ የመንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ሥራዎች ማለቂያ የለሽ ቢሆኑም እንኳን፣ ለማብራራት ያህል ግን ትኩረታችንን በጥቂት ወሳኝ በሆኑ ምሳሌዎች ላይ እናደርጋለን፡፡

በመጀመሪያ፣ መንፈስ ቅዱስ የቅዱሳት መጻሕፍትን አብርሆት ሰጥቷል፣ ያም የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ቃል የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን በመገንዘብ መንፈስ ቅዱስ ራሱ አምላክ መሆኑን እውቅና እንሰጣለን፡፡ ይህንንም ሃሳብ በማቴዎስ ምዕራፍ 10 ቁጥር 20፣ ዮሐንስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 34፣ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1 ቁር 16 እና ምዕራፍ 4 ቁጥር 31 እና ኤፌሶን ምዕራፍ 6 ቁጥር 17 ላይ እናገኛለን፡፡

አንድ ምሳሌ ለመውሰድ ያህል፣ በ2ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 20 እና 21 የጴጥሮስን ንግግሮች አድምጡ፡

ይህን በመጀመሪያ እወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ

ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፤
ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር
ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።
(2ጴጥ 1፥20-21)

በዚህ ምንባብ፣ በመንፈስ ቅዱስ መነዳት ማለት ከእግዚአብሔር የሆነውን መናገር ማለት እንደሆነ ጴጥሮስ አስተምሯል፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔር ቃል ናቸው ምክንያቱም አብርሆተ እግዚአብሔር ያለባቸውና እግዚአብሔር የተናገራቸው ናቸው፣ በተለይም፣ ሦስተኛው የእግዚአብሔር ስብዕና የመንፈስ ቅዱስ አብርሆት አለባቸው፡፡

ሌላ ምሳሌ ለመውሰድ፣ መንፈስ ቅዱስ እንደ አማካሪ የሚሠራው ሥራ መለኮትነቱን ያሳያል፡፡ በዮሐንስ ምዕራፍ 14 እስከ 16 እንደምንመለከተው፣ መንፈስ ቅዱስ እውነትን የመግለጥ፣ ዓለምን ስለ ኀጢአት የመውቀስ፣ ስለ ኢየሱስ የመመስከርን የማማከር ሥራዎች እንደሚሠራ ኢየሱስ ተናግሯል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ስንሰማው ግር የሚያሰኝ ቢመስልም፣ ይህ አገልግሎት መንፈስ ቅዱስን ከኢየሱስ በምድር መገኘትም የተሻለ ዋጋ እንዳለው አመልክቷል፡፡ በዮሐንስ ምዕራፍ 16 ቁጥር 7 ኢየሱስ እንዲህ ተናግሯል፡-

እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ፤ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል። እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልከላችኋለሁ።
(ዮሐ 16፥7)

ስለዚህ ነገር ጥቂት ቆም ብላችሁ አስቡ፡፡ ኢየሱስ ራሱ እንደተናገረው፣ ኢየሱስ ራሱ በምድር ከመገኘቱ ይልቅ ቤተክርስቲያን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር መገለጧ የተሻለ ነው፡፡ ግን ፍጡር፣ የተገደበ ምንነት የክርስቶስን የምድር አገልግሎት በተሻለ መንገድ ሊያከናውን አይችልም፡፡ በፍፁም አይታሰብም፣ መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ወልድ የበለጠ ጠቀሜታን ይሰጥ ዘንድ፣ እርሱ ራሱ አምላክ ሊሆን ይገባዋል፡፡

# ቀመሮች

ቅዱሳት መጻሕፍት የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት ከሚያረጋግጡባቸው መንገዶች አራተኛው ስሙ ከአብ እና ከወልድ ጋር የመጠቀሱ የስላሴ ቀመር ነው፡፡

የስላሴ ቀመር በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የስላሴ ሦስቱም አካላት በእኩል ተቀራራቢ መሠረት፣ በተለይም የእነርሱን ቅንጅት በመግለጥ የተጻፉባቸው ምንባቦች ናቸው፡፡

እግዚአብሔር አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አቻ ባለድርሻዎች መሆናቸውን በመግለጥ፣ መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ እንደ አብና እንደ ወልድ ሁሉ መለኮት መሆኑን ያመለክታል፡፡ እነዚህንም ቀመሮች በሮሜ ምዕራፍ 15 ቁጥር 30፤ 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12 ከቁጥር 4 እስከ 6፤ 2ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ 2 ቁጥር 13 እና 14 እና በሌሎችም በርካታ ቦታዎች እናገኛቸዋለን፡፡ ከነዚህ ቀመሮች ሁለት ማሳሌዎችን ብቻ እንመልከት፡፡

የመጀመሪያው በማቴዎስ ምዕራፍ 28 ቁር 19፣ ኢየሱስ ይህንን ትዕዛዝ በሰጠበት ውስጥ ይገኛል፡

> እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥... (ማቴ 28፥19)

በዚህ ቀመር፣ ጥምቀት በሦስቱም የስላሴ አካላት ሥልጣን ሊከናወን እንደሚገባ ኢየሱስ አመልክቷል፡፡ ይህ ትዕዛዝ በስላሴ አካላት ዘንድ ምንም የከበሬታ ልዩነት እንደሌለ አመልክቷል፡፡ ሦስቱም እኩል መሆናቸውን ግን ገልጧል፡፡

ሁለተኛው ግልጽ ምሳሌ ደግሞ ጳውሎስ እነዚህን ቃላት በተናገረባቸው በ2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 13 ቁጥር 14 ላይ ይገኛል፡

> የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን። አሜን። (2ኛቆሮ 13፥14)

የመልእክቱ መደምደሚያ በሆነው የስንብት ሰላምታ፣ ጳውሎስ ቢጋራ አስቀምጧቸዋል፡ ወልድን፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚል ስም ሰጥቶት፤ አብን፣ አግዚአብሔር ብሎ ጠቅሶትና መንፈስ ቅዱስን በቀጥታ፡፡ ይህንንም በማድረግ፣ ሦስቱም አካላት የድነትን በረከት በእኩልነት የሚሰጡ አድርጎ አቅርቧቸዋል፡፡

እነዚህን የመሳሰሉ ቀመሮች መንፈስ ቅዱስ በስላሴ ውስጥ እኩያ ስብዕና ያለው መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ወሳኝ መለኮታዊ ባህርያትን እና እንቅስቃሴዎችን፣ ለምሳሌ ለኀጢአተኞች ፀጋንና ድነትን በመስጠት፣ እንደ አምላክም ክብርንና አምልኮን በመቀበል እኩል መሆናቸውን ያመለክታሉ፡፡

> *የክርስቲያን ትምህርተ ስላሴ አንዱ አምላክ በአንድነት ሦስትነት ለዘላለም እንደሚኖር ያስተምራል፡፡ መንፈስ ቅዱስ አምላክ በመሆኑ፣ ወደ እርሱ መጸለይ ብቻ ሳይሆን፣ እንደ አምላክነቱም ማክበር ተገቢ ነው፡፡ [ዶ/ር ኬት ጆንሰን]*

የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት ከተመለከትን፣ ወደ ሁለተኛው ርዕሳችን፡ ወደ ስብዕናው ለመዛወር ዝግጁ ነን፡፡ በዚህ ትምህርት፣ መንፈስ ቅዱስን እውነተኛ ስብዕና እንዳለው እንጂ መለኮታዊ ኃይል ወይንም ጉልበት እንደሆነ ብቻ ልንቀርበው የማይገባ የመሆኑን እውነታ እንመለከታለን፡፡

# 3. ስብዕና

በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ፣ በርካታ ቡድኖች መንፈስ ቅዱስ የራሱ የሆነ ግላዊ-መለያ እና የመለኮታዊ ስብዕና ባህርያት የሉትም ብለው ይክዳሉ፡፡ ጥቂቶቹ ደግሞ የአብ ሌላኛው ቅርፅ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ "መንፈስ ቅዱስ" የሚለው ስም የጥንት ጸሐፍት ለእግዚአብሔር ኃይል የሚጠቀሙበት መጠሪያ ብቻ ነው በማለት ይሟገታሉ፡፡ ግን ከሐዋያት የሃይማኖት መግለጫ አወቃቀር፣ መንፈስ ቅዱስ እውን እና የራሱ የሆነ ስብዕና ያለው አምላክ ነው የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥፍራውን እንመለከታለን፡፡ ይህም የቅዱሳት መጻሕፍት ግልፅ አስተምህሮ ሲሆን፣ በዘመናት ሁሉ የሚገኙ የአብያተክርስቲያናት ቅርንጫፎችም ሁሉ ተገቢ ስፍራው እንደሆነ ይታመንበታል፡፡

> *መንፈስ ቅዱስ በአዲስ ኪዳን ስብዕና ያለው አካል በሚገለጥበት መንገድ እንጂ አካላዊ ኃይል ብቻ እንደሆነ አልተገለጠም፡፡ የተቀሩትም አብያተ ክርስቲያናት በዚህ ምስክርነት ዙሪያ የሚሰባሰቡ ሲሆን እኛም የምናምነው በዚሁ ነው፡፡ ይህንን ሃሳብ ግልጽ በሆነ መንገድ በኋለኞቹ የሃይማኖት መግለጫዎች ለመግለጥ ከመሞከሩና ግልፅ የሆነ ሙግት ከመቅረቡ አስቀድሞ ሦስት ወይም አራት መቶ ዓመታት ወስዷል፡፡ የቂሳርያው ባሲል ጉዳዩን በአራተኛው ምዕተ-ዓመት ሲያነሳው፣ አዲስ አስተምህሮ አላነሳም፣ ያደረገው ለሦስት መቶ ዓመታት ሰዎች ያምኑበት የነበረውን ነገር ወደ አደባባይ ማውጣት ብቻ ነው፡፡ [ዶ/ር ፒተር ወከር]*

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው ከዚህ አንፃር ነገሩን በይፋ ነጥሎ እንዳልተናገረበት ልናምን ይገባል፡፡ ግን ስለ መንፈስ ቅዱስ በክርስትና የመጀመሪያዎቹ ምዕተ-ዓመታት የተደረጉትን ነገረ-መለኮታዊ ሙግቶች ስንመለከት፣ መንፈስ ቅዱስ የስላሴ አካል ነው በማለት የሃይማኖት መግለጫው የሰጠው ማረጋገጫ የእርሱንም ስብዕና የሚያረጋግጥ እንድምታ ይዟል፡፡ በቀረውም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ መንፈስ ቅዱስን ወደ መለኮታዊ ኃይል ብቻ በማውረድ ስብዕናውን የማቃለልን ነገር በብርቱ ውድቅ አድርጎታል፡፡

የሃይማኖት መግለጫው ስለ መንፈስ ቅዱስ ስብዕና የሰጠውን ማረጋገጫ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ስንመረምር፣ ውይይታችን በሦስት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ በመጀመሪያ፣ መንፈስ ቅዱስ

የያዘውን ሰብዓዊ የባህርይ መገለጫ እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ ከአብና ከወልድ በሚለይበት ስብዕና ላይ እናተኩራለን፡፡ ሦስተኛ፣ ከሌሎቹ የስላሴ አካላት ጋር ያለውን ዝምድና እንመለከታለን፡፡ መንፈስ ቅዱስ ምሉዕ ስብዕና ያለው መሆኑን በሚያረጋግጡ የባህርይ መገለጫዎች እንጀምራለን፡፡

## የባህርይ መገለጫዎች

ስለ መንፈስ ቅዱስ ሰብዓዊ የባህርይ መገለጫዎች ስንነጋገር፣ አንድ ስብዕና ያለው አካል ብቻ ሊኖረው የሚችለውን መለያዎች ማለትም እርሱ በእውን ስብዕና ያለው እንጂ እንዲያው ስብዕና የሌለው ኃይል ብቻ ካልሆነ የሚኖረውን ባህርይ በአዕምሯችን ይዘን ነው፡፡

> *አዲስ ኪዳን ስለ እግዚአብሔር አብ ስሞችና ማዕረጎች ብቻ፣ የእግዚአብሔር አብን ሥራዎች ብቻ፣ የእግዚአብሔር አብን የባህርይ መገለጫዎች ብቻ፣ የእግዚአብሔር አብን ድርጊት ብቻ፣ ሳይሆን ስለ ወልድ እና ስለ መንፈስ ቅዱስም በተመሳሳይ መንገድ መግለጡ እጅግ ገንቢ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ በሌላ ቃል፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ለእግዚአብሔር አብ የሚሰጣቸው ሰብዓዊ መገለጫዎች ሁሉ በአዲስ ኪዳንም ለመንፈስ ቅዱስ ተገልጠው እናገኛቸዋለን፡፡ እንግዲህ ይህ፣ እንደገና፣ መንፈስ ቅዱስ ኃይል ወይም ጉልበት ብቻ ሳይሆን ስብዕና ያለው መሆኑን አፅንዖት እንድንሰጥ ያደርገናል፡፡ [ዶ/ር ጄ. ሊጎን ዱንካን ሳልሳዊ]*

መንፈስ ቅዱስ ዘርዝረን የማንዘልቃቸው ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሰብዓዊ መገለጫዎች ያሉት በመሆኑ ሁሉንም በዚህ ትምህርት ልናካትት አንችልም፣ ስለዚህ የእርሱን ስብዕና ለመግለጥ አራት ምሳሌዎችን ብቻ እናቀርባለን፡፡ መንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ያለው መሆኑን በመናገር እንጀምራለን፡፡ ይህም ለማቀድ፣ ለመሻትና ለመምረጥ የሚችልበት ማንነቱ ነው፡፡ በግልፅ ስንናገር፣ እነዚህ ነገሮች ያሉት ማንኛውም ሰው በምንም መንገድ እንዲሁ ኃይል ወይም ጉልበት ብቻ ሊሆን አይችልም፡፡ ፈቃድ ያለው የመሆኑን አንድ ምሳሌ ለማንሳት ያህል፣ ጳውሎስ ስለ ጸጋ ስጦታዎች መታደል የተናገረበትን 1ኛቆሮንቶስ ምዕራፍ 12 ቁጥር 11 እንመልከት፡

> ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል። (1ቆሮ 12፥11)

መንፈስ ቅዱስ አንዳንድ ሰዎች የተወሰኑ ስጦታዎች እንዲኖራቸው ሌሎቹ ደግሞ ሌሎች ስጦታዎች እንዲኖሯቸው ይፈልጋል፡፡ ስብዕና የሌላቸው ነገሮች ዕቅድና መሻት ሊኖራቸው

አይችልም፡፡ ስብዕና ያላቸው ብቻ ናቸው፡፡ እንግዲያው መንፈስ ቅዱስ ስብዕና ያለው ሊሆን ግድ ነው፡፡

መንፈስ ቅዱስ በተጨማሪም የማወቅ ባህርይ አለው፣ ያም ሌሎችን ለመስተማር የሚችልበት እውቀት ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህንንም እውቀት በብዙ መንገድ ይገልጠዋል፡፡ 1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 10 እስከ 12 ያለውን ስናነብብ የእግዚአብሔርን ልቡና በመሻትና በማወቅ እና ሮሜ ምዕራፍ 8 ቁጥር 27ን ስናነብብ የራሱንም ልቡና በመያዝ ይገልጠዋል፡፡ 1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12 ቁጥር 8 ላይ እንደምናነብበው ጥበብንና ዕውቀትን ይሰጣል፡፡ በሉቃስ ምዕራፍ 12 ቁጥር 12 እንደተገለጠው ደግሞ ያስተምራል፡፡

በዮሐንስ ምዕራፍ 14 ቁጥር 26 ላይ ደግሞ ኢየሱስ ራሱ ስለመንፈስ ቅዱስ እውቀት ተናግሯል፡፡ ለሐዋርያቱ የተናገረውን አድምጡ፡

> አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል። (ዮሐ 14፥26)

ስብዕና የሌላቸው ኃይላት ሊያስቡ፣ ሊያውቁና ሊያስተምሩ አይችሉም፡፡ እንግዲያው፣ የእውቀት ባህርይ መንፈስ ቅዱስ አካል መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

መንፈስ ቅዱስ በተጨማሪም ለሌሎች አካላትና ሁነቶች ምላሽ የሚሰጥበት ስሜት እና ውስጣዊ መነካት አለው፡፡ እንደሌሎቹ ሰብዓዊ ባህርያት ሁሉ፣ ስሜቱም ስብዕና ያለው እንጂ እንዲያው ኃይል ብቻ አለመሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ለምሳሌ፣ የመንፈስ ቅዱስ ፍቅር በሮሜ ምዕራፍ 15 ቁጥር 30 ተገልጧል፡፡ ደስታው ደግሞ በ1ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ 1 ቁጥር 6 የእርሱ ደስታ ተነግሯል፡፡ በኤፌሶን ምዕራፍ 4 ቁጥር 30 ስለ ሃዘኑ እንዴት እንደተናገረ አድምጡ፡

> ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ። (ኤፌ 4፥30)

መንፈስ ቅዱስ ሃዘንን የመሰለ ስሜት ያለው የመሆኑ እውነታ እርሱ በእውነት ስብዕና ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ፣ መንፈስ ወኪል ብለን የምንጠራው የባህርይ መገለጫም ባለቤት ነው፡፡ ነገሮችን እንደ ወደደ የሚያደርግበትና የሚወስንበት ፈቃድም አለው፡፡ ይህም በሰብዓዊያን ብቻ ሊከናወኑ የሚችሉ በርካታ ተግባራትን እንዲያከናውን ያግዘዋል፡፡ ለአብነት ያህል፣ መንፈስ ቅዱስ በዮሐንስ ምዕራፍ 15 ቁጥር 26 እና በሮሜ ምዕራፍ 8 ቁጥር 16 ላይ

እንደምናነብበው ስለ ጌታ ይመሰክራል፡፡ በፊልጵስዩስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 1 ላይ እንደምናየው ከእኛ ጋር ኅብረት ያደርጋል፡፡ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ቁጥር 29 እና ምዕራፍ 13 ቁጥር 2 ውስጥ ደግሞ ይናገራልም ያዛልም፡፡

አንድ ምሳሌ ለማንሳት፣ ሮሜ ምዕራፍ 8 ቁጥር 26 እና 27 የሚናገረውን አድምጡ፡

> እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤
> ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና። (ሮሜ 8፥26-27)

መንፈስ ቅዱስ ስለ አማኞች የሚማልድ የመሆኑ እውነታ ለእርሱ ስብዕና ሌላው ማረጋገጫ ነው፡፡ ስብዕና የሌላቸው ኃይላት ልባዊ የሆነ ጸሎትን ሊጸልዩ፣ ሊማልዱና ሊቃትቱ አይችሉም፡፡ እነዚህን ነገሮች ማድረግ የሚችሉ ስብዕና ያላቸው ብቻ ናቸው፡፡

ከ1834 እስከ 1892 የኖረው ታላቁ የባፕቲስት ሰባኪ ቻርለስ ስፐርጀን፣ ሮሜ ምዕራፍ 8 ቁጥር 26 እና 27 መሠረት አድርጎ The Holy Spirit's Intercession, በሚል ርዕስ በሰበከው ስብከት በዚህ መንገድ ተናግሯል፡፡ እስኪ የተናገረውን አድምጡ፡

> *መንፈስ ቅዱስ  የአካል ህመም ቢሆን፣ የአዕምሮ ጭንቀት ቢሆን፣ መንፈሳዊ ውጊያ ቢሆን፣ የስማችን መጥፋት ቢሆን፣ ድህነት ቢሆን መከራ የአካላችንንና የልቡናችንን ደካማነት እንድንሸከም፤ መስቀላችንንም እንድንሸከም ያግዘናል፡፡ ድካማችንን ያግዛል፤ ረድኤታችን መለኮታዊ ብርታት ስላለው ውጤቱ አያስፈራንም፡፡ የእግዚአብሔር ፀጋ በቂያችን ነው፤ ኃይሉም በድካማችን ይፈፀማል፡፡ [ቻርለስ ስፐርጀን]*
>
> *በእኔ ውስጥ ከእኔ እጅግ የሚልቅ ኃያል፣ በእኔ ውስጥ በሥራ ላይ ያለ አንድ አካል መኖሩን ማወቅ በጣም ያበረታል፡፡ ምንም እንኳን አንዳንድ ጊዜ ረድኤት የሌለኝ መስሎ ቢሰማኝም፣ ባርነት ቢሰማኝም፣ ብቻ ምንም ይሁን ምን ያ የስሜት ቋንቋ ብቻ ነው እንጂ እውን አይደለም፡፡ ሁሉን ቻዩ የእግዚአብሔር መንፈስ እኔ ክርስቶስን እንድመስል ለማድረግ ያለ እረፍት በሥራ ላይ ነው፡፡ ምንኛ ድንቅ የሚያበረታ ነገር ነው! በተጨማሪም እኔ ዘወትር በሕያው እግዚአብሔር ኅልውና ውስጥ መኖሬ፣ ዘወትር በእግዚአብሔር ፊት መኖሬ እጅግ የሚያረሰርስ ነው፡፡ ምንም እንኳን ድካሞቻችንን ከሌሎች ሰዎች ብንሸሽግም፣ የተሰወረ ኃጢአት ብሎ ነገር ግን የለም ምክንያቱም የምኖረው በእግዚአብሔር ኅልውና ውስጥ ነውና፡፡ መንፈስ ቅዱስም ቅዱስ መንፈስ ነው፤*

*የእግዚአብሔር መንፈስ ንፁህ ነው፡፡ እንደ እረኛ ከኀጢአት ጋር በመታገል ላይ ያሉ ሰዎችን ሳማከር ይህንን ሚዛን ማስጠበቅ በእርግጠኝነት እሻለሁ፡፡ ተስፋ ቢሶች አትሁኑ፡፡ መንፈስ ቅዱስ በልባችሁና በሕይወታችሁ ውስጥ በሥራ ላይ ነው ስለዚህም ከኀጢአት ጋር በምታደርጉት ትግል ድልን እንደሚሰጣችሁ በማመን በክርስቶስ እርፍ በሉ፡፡ መንፈስ ቅዱስ ዘወትር በሥራ ላይ ስለሆነና ዛሬም በውስጣችሁ ስለሚኖር ብቻችሁን የሆናችሁ አይምሰላችሁ፡፡ [ዶ/ር ዴኒስ ጆንሰን]*

የመንፈስ ቅዱስ ሰብዓዊ የባህርይ መገለጫዎች የእርሱን ስብዕና እንዴት እንዳረጋገጡ ስለተመለከትን፣ ከአብና ከወልድ የሚለይባቸውንና በስላሴ ውስጥ ራሱን የቻለ አካል መሆኑን እንመለከታለን፡፡

# ልዩነት

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በመንፈስና በሌሎቹ የስላሴ አካላት መካከል ያለው ልዩነት በግልፅ ያልተቀመጠባቸው በርካታ ምንባቦች መኖራቸውን በማመን እንጀምራለን፡፡ ለምሳሌ፣ መንፈስ ቅዱስ በገላትያ ምዕራፍ 4 ቁጥር 6 ላይ የልጁ መንፈስ ተብሎ ተገልጧል፣ በማቴዎስ ምዕራፍ 10 ቁጥር 20 ላይ ደግሞ የአብ መንፈስ ተብሎ ተጠቅሷል፡፡ መለያዎቻቸውን ከማሳየት ይልቅ፣ ከሌሎቹ የስላሴ አካላት ጋር ያለውን ዝምድናዊ ግንኙነት የሚያጎሉ በርካታ መጠሪያዎች አሉት፡፡

ምንም እንኳን እነዚህን የመሳሰሉ ምንባቦች በቀደመችው ቤተክርስቲያን ውስጥ ለበርካታ ሙግቶች ምክንያት ቢሆኑም፣ እነዚህ ጥብቅ ቁርኝቶች ሊያስገርሙን ግን አይገባም፡፡ በመሠረቱ ሦስቱም የስላሴ አካላት አንድ አምላክ ናቸው፡፡ እንግዲያው፣ መንፈስ ቅዱስን የአብና የወልድ መንፈስ እንደሆነና እርሱ ራሱም ደግሞ ከሌሎቹ አካላት የሚለይበት ስብዕና እንዳለው ማሰብ ያልተዛባ ትርጉም የሚሰጥ ነገር ነው ማለት ነው፡፡

በመንፈስና በሌሎቹ የስላሴ አካላት መካከል ያለውን መለያ የምናሰምርበት አንዱ መንገድ አንዳቸው ከሌላቸው ጋር ያላቸውን መለያ በሚገልጥ መንገድ እርስ በርስ የሚነጋገሩባቸውን ምንባቦች መመልከት ነው፡፡ እነዚህን መለያዎች የሚያሳዩ በርካታ ምንባቦች ቢኖሩም፣ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር የሚለይበት መለያ እንዳለው ለማሳየት ሁለቱ ይበቁናል፡፡ በመጀመሪያ፣ ኢየሱስ በዮሐንስ ምዕራፍ 16 ቁጥር 7 ላይ የተናገረውን እንይ፡-

> እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ፤ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል። እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ። (ዮሐ 16፥7)

ኢየሱስ በዚህ ስፍራ እየተናገረ ያለው ወልድ ካልሄደ በስተቀር መንፈስ ቅዱስ እንደማይመጣ ነው፡፡ ሌላው ከመምጣቱ አስቀድሞ ሌላው ሊሄድ እንደሚገባው በመናገር ኢየሱስ ራሱን ከመንፈስ የተለየ መሆኑን በግልጽ ተናግሯል፡፡ እያንዳንዳቸው የተሰጣቸው ድርሻ አለ፣ ስለዚህም ወልድ የምድር አገልግሎቱን ፈጽሞ ወደ ሰማይ እስካላረገ ድረስ የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ አይጀመርም፡፡ ይህም መንፈስ ከወልድ የሚለይ መሆኑን ግልፅ ያደርገዋል፡፡

በተመሳሳይም መንገድ፣ መንፈስ ከአብ የሚለይበትን ሥራም ይሠራል፡፡ ለምሳሌ፣ መንፈስ ቅዱስ እንደ አማካሪነቱ፣ የእኛ ተከላካይ ጠበቃ በመሆን፣ ጉዳያችንን በእግዚአብሔር ፊት በማቅረብ በጸሎታችንም በማገዝ ይማልድልናል፡፡

*በጥቅሉ፣ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የክርስቶስን ሥራ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ ክርስቶስ የእኛ መስዋዕት ሆኖ ሕይወቱን ሰጠን፡፡ ያንንም ሥራውን በእኛ ሕይወት መተግበር የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው፡፡ ስለዚህ ሁለቱም ያስፈልጉናል፡፡ ማለትም እግዚአብሔር ለእኛ ያቀደውና በክርስቶስ የሠራው ሥራ ከውስጥ እንድንለወጥ የሚያደርግ ስለሆነ መንፈስ ቅዱስ ከሌለን ተግባራዊ ማድረግ ስለማንችል በጥሩ አቋም ላይ አንሆንም፡፡ ስለዚህም መንፈስ ቅዱስ ይመጣል መንፈስ አዲስ ልደትንም ይሰጠናል፡፡ መንፈስ ይቀድሰናል መንፈስ ዘወትር ስጦታዎችን፣ በረከቶችንና ፍሬዎችን በሕይወታችን ይሰጠናል፣ በዚህ ሁሉ የመንፈስ ሥራ ከቶውኑ ምትክ የለሽ ሥራ ነው፡፡ [ዶ/ር ጆን ፍሬም]*

ለምሳሌ፣ በሮሜ ምዕራፍ 8 ቁጥር 26 እና 27 ላይ ጳውሎስ እነዚህን ቃላት ጽፏል፡

እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤
ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና።

መንፈስ ቅዱስ በአብ ፊት ይማልድልናል በማለት ጳውሎስ ሲያስተምር፣ ሁለቱም የተለያየ ስብዕና ያላቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡ አንዱ ይማልዳል፣ ሌላው ደግሞ ምልጃውን ይቀበላል፡፡

*ወደ አብ ይማልድልናል፡፡ ጳውሎስ እንደሚናገረውም፣ እንዴት መጸለይ እንዳለብን ስለማናውቅ ልንጸልይ የተገባንን በልባችን ያፈስሳል፣ በውስጣችንም ይቃትታል፡፡ ስለዚህ እኛ ምን ማለት እንዳለብን የማናውቃቸውን ነገሮች ለእግዚአብሔር እንድንናገር ያስችለናል፡፡ [ዶ/ር ጆን ፍሬም]*

*የተለመደው የፀሎት አቀራረብ በልጁ በኢየሱስ ስም እና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወደ አብ መጸለይ ነው ልትሉ ትችላላችሁ፡፡ ይህም ሆኖ ግን የእግዚአብሔርን ክብር ሳንነካና የጸሎታችንን ላዕላይ መድረሻ ሳናቃልል ወደ መንፈስ ቅዱስ ወደ ራሱ በቀጥታ በሚለመንበት የጸጋና የነፃነት ሃይማኖት ውስጥ እንገኛለን፡፡ [ዶ/ር ግሌን ስኮርጂ]*

ከ354 ዓ.ም. እስከ 430 ዓ.ም. የኖረው የቤተክርስቲያን አባት የአውጉስቲን እንደሆነ የሚነገርለት፣ ቀጥሎ የምንመለከተው ለመንፈስ ቅዱስ የቀረበ ጸሎት፣ ለግል ጸሎታችን ተምሳሊት የሚሆን አስደናቂ ነገር ይሰጠናል፡፡

*አ መንፈስ ቅዱስ ሆይ፣ እስትንፋስህን ስጠኝ፣*

*ያን ጊዜም ሃሳቦቼ የተቀደሱ ይሆናሉ፤*

*አ መንፈስ ቅዱስ ሆይ፣ በውስጤ ሥራ፣*

*ሥራዎቼም የተቀደሱ ይሆናሉ፤*

*አ መንፈስ ቅዱስ ሆይ፣ ልቤን ወደ አንተ ሳብ፣*

*በተቀደሰ መንገድም መውደድ እችላለሁ፤*

*አ መንፈስ ቅዱስ፣ አበርታኝ፣*

*የተቀደሰውን ሁሉ መጠበቅም እችላለሁ፤*

*አ መንፈስ ቅዱስ፣ ከልለኝ፣*

*እኔም ዘወትር እቀደሳለሁ፡፡*

መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር ያለውን መለያ በስብዕናዊ ባህርያቱ ስንመለከት ቆይተናል፣ አሁን ደግሞ ከሌሎቹ የስላሴ አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት እንመልከት፡፡

# ግንኙነት/ዝምድና

በዚህ ትምህርት ከዳር እስከዳር እንዳነሳነው፣ በስላሴ አካላት ዘንድ ያለው ግንኙነት በትውፊታዊ መንገድ በሁለት የተለያዩ አመለካከቶች ይገለፃል፡፡ በተለይም፣ የነገረ መለኮት ምሁራኑ ስለ ኦንቶሎጂያዊ ስላሴና ስለ ኤኮኖሚያዊ ስላሴ ይናገራሉ፡፡ ሁለቱም አመለካከቶች ስለዚያው ስለ ስላሴ ስለ አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የሚናገሩ ናቸው፡፡ ግን ከእነዚህ ሦስት መለኮታዊ አካላት ግንኙነት አንፃር በተለያዩ አመለካከቶች ላይ አፅንኦት ይሰጣሉ፡፡

ስለ ኦንቶሎጂያዊ ስላሴ ስንነጋገር፣ በእግዚአብሔር ማንነትና ኑባሬ ላይ ማትኮራችን ነው፡፡ በዚህ አመለካከት፣ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር በኃይልና በክብር አንድ ነው፡፡ ሦስቱም የእግዚአብሔር አካላት የማይገደቡ፣ ዘላለማዊ እና የማይለዋወጡ ናቸው፡፡

እያንዳንዳቸውም ተመሳሳይ ወሳኝ ባህርያት፣ ማለትም ጥበብ፣ ኃይል፣ ቅድስና፣ ፍትህ፣ መልካምነትና እውነት አሏቸው፡፡

ስለ ኤኮኖሚያዊ ስላሴ ስንነጋገር ደግሞ፣ ሦስቱ የእግዚአብሔር አካላት እርስ በእርስ እንዴት እንደሚገናኙ ትኩረት እንሰጣለን፡፡ በዚህ አመለካከት፣ ሦስቱም የእግዚአብሔር አካላት፣ የተለያየ ሃላፊነት አላቸው፣ የተለያየ ሥልጣን አላቸው እናም የየራሳቸው ተግባርም አላቸው፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን ለአብና ለወልድ ሥልጣን የሚገዛ ነው፡፡ በዋናነትም የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ የእነርሱን መመሪያ ማስተላለፍና እነርሱን ማክበር ነው፡፡

> *እግዚአብሔር ባለበት ሁሉ፣ መንፈሱ በዚያ አለ፡፡ መንፈሱ መገኘቱን ብቻ ሳይሆን፣ ተግባሩንም ያመለክተናል፡፡ እናም እግዚአብሔርም ከፍጥረቱ ጋር ግንኙነት የሚያደርግበትን መንገድ ስትከታተሉ፣ ያንን ከመንፈስ ቅዱስ ውጪ መግለጥ የማይቻል ነው፡፡ አሁን የሰውን ታሪክ የሚመራው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን የአብሮነት ክብካቤና ፍቅር የሚያሳይ እውነተኛ ወኪል ነው፡፡ [ዶ/ር አልበርት ሞህለር]*

በክርስቲያናዊ ነገረ መለኮት፣ በኦንቶሎጂካል ስላሴ ወይንም በኤኮኖሚያዊ ስላሴ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ሦስተኛው አካል ተብሎ ይጠራል፡፡

የኦንቶሎጂካል ስላሴ ሦስተኛ አካል ነው ምክንያቱም የመጀመሪያው አካል የሆነው የአብ እና ሁለተኛ አካል የሆነው የወልድ እስትንፋስ ስለሆነ ነው፡፡ አሁን ቆም ብለን፣ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተክርስቲያናት መንፈስ ቅዱስ የአብ እንጂ የወልድ እስትንፋስ አይደለም ብለው የሚያስተምሩ መሆኑን መናገር ይገባናል፡፡ ይህ የአስተምህሮ ልዩነት በ1054 ዓ.ም. (እ.ኢ.አ) በምሥራቅና በምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የተፈጠረውና እስካሁን የዘለቀው ልዩነት አንዱ ምክንያት ነው፡፡ እርግጥ ነው፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው ከዚህ ውዝግብ በፊት ስለወጣ፣ ይህንን በምስራቅና በምዕራብ መካከል የተፈጠረ አለመስማማት መፍትሄ አልሰጠውም፡፡ ሁለቱም የቤተክርስቲያን ቅርንጫፎች የሐዋርያትን የሃይኖት መግለጫ ይቀበላሉ፡፡

ከኤኮኖሚያዊ ስላሴ አንፃር ደግሞ፣ መንፈስ ቅዱስ ሦስተኛ አካል ይባላል ምክንያቱም ለአብና ለወልድ ራሱን በመስጠት ሦስተኛው እርከን ላይ ስለሚገኝ ነው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ይህንን መሰጠቱን በብዙ መንገድ ይገልጡታል፡፡ ለአብነት፣ በአብና በወልድ መላኩ፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ይህንን በሉቃስ ምዕራፍ 11 ቁጥር 13፣ ዮሐንስ ምዕራፍ 14 ቁጥር 26 እናምዕራፍ 15 ቁጥር 26፣ እና የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ቁጥር 33 ላይ ጠቅሰውታል፡፡ በመጣ ጊዜም፣ መንፈስ ቅዱስ አብና ወልድ እንዲከናውን የሰጡትን በመፈፀም ታዝዟል፡፡ ይህንንም በዮሐንስ ምዕራፍ 16 ቁጥር 13፣ ሮሜ ምዕራፍ 8 ቁጥር 11 እና 1ጴጥሮስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 2 ላይ እንማራለን፡፡

እርግጥ ነው፣ መንፈስ ቅዱስ በኤኮኖሚያዊ ስላሴ አተያይ ዝቅተኛውን እርከን የያዘ ቢሆንም፣ እርሱ ግን ፍፁም አምላክ እና በፍጥረት ሁሉ ላይ ሉዓላዊ ሥልጣን ያለው መሆኑን አፅንኦት

መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚም ባሻገር፣ በስላሴ ውስጥ፣ አንዱ የሚሠራውን ሌላውም እስካከናወነው ድረስ፣ በመካከላቸው በመግባባት የሚገለጥ ልዩነት አለ፡፡ እንግዲያው፣ የመንፈስ ቅዱስ ለአብና ለወልድ መስጠት ከእነርሱ የሚያንስ ነው ማለት በፍፁም አይደለም፡፡ ከእነርሱ ወሳኝ መለኮትነት ጋር እኩል ነው፡፡

የመንፈስ ቅዱስ ስብዕና የክርስቲያናዊ ነገረ-መለኮት እጅግ አስፈላጊ ክፍል ነው፡፡ እንደተመለከትነውም፣ ልናረጋግጠው የሚገባባቸውም በርካታ ምክንያቶች አሉን፡፡ መንፈስ ቅዱስ ራሱን የቻለ፣ የራሱ ስብዕና ያለው መሆኑን የሚያመለክቱ የባሕርይ መገለጫዎች አሉት፡፡ ስለዚህ እርሱ ከአብና ከወልድ ጋር ያለው ግንኙነት ስብዕና ያለው እንጂ እንዲያው ዝም ብሎ ኃይል ወይም ጉልበት ብቻ እንደሆነ እንዲታሰብ ምንም ቀዳዳ አይከፍትም፡፡ በዚህ ትውፊታዊ አስተምህሮ ትልቅ መተማመን አለን፡፡

በዚህ ስለ መንፈስ ቅዱስ በተማርነው ትምህርት፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ የመንፈሱን መለኮትነት እና ፍፁም ሰውነት ያረጋገጠ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ አሁን ደግሞ፣ ሦስተኛውን ርዕሳችንን ማለትም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በታሪክ ዘመናት መካከል የተከናወነና ዛሬም እየተከናወነ ያለ መሆኑን እናነሳለን፡፡

# 4. ሥራ

*ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ በጥልቀት ከማወቁ በረከቶች አንዱ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ግለሰባዊ በሆነ መንገድ እየሠራ መሆኑን ለማወቅ ማስቻሉ ነው፡፡ ከሆነ ስፍራ ሆኖ የመብራትን ማብሪያና ማጥፊያ እንደመንካት ዓይነት ሥራ አይሠራም፡፡ ወደ እኛ በመምጣት በግል ከእያንዳንዳችን ጋር ግንኙነት ያደርጋል፡፡ ስለዚህም መንፈስ ቅዱስ በልባችን ያድራል፡፡ ከእኛ ጋር እና ለእኛ ይጸልያል፡፡ ይቀድሰናል ደግምም በበርካታ መንገዶች ከእኛ ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ በመሠረቱም ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች እንደተናገረው፣ በእያንዳንዲቷ የሕይወታችን እርከን ክርስቲያናዊ ፍሬዎችን ይሰጠናል፡፡ በቤተክርስቲያን የምናገለግልባቸውን በርካታ ስጦታዎች ይሰጠናል፣ ይህም እግዚአብሔር በመንፈሱ በውስጣችን የሚሠራው ሥራ ነው፡፡ [ዶ/ር ጆን ፍሬም]*

ምንም እንኳን የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው “በመንፈስ ቅዱስ አምናለሁ” በማለት ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ነጥሎ የተናገረው ብዙ ባይኖርም፣ መግለጫው በመነሻው ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ በርካታ የእምነት አቋሞችን አንፀባርቋል፡፡

የመንፈስ ቅዱስን ሥራ የምንገልጥባቸው በርካታ መንገዶች አሉ፣ ግን እኛ በአራቱ ላይ ብቻ እናተኩራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ አስቀድመን የፈጣሪነት ኃይሉን እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ በመቀደስ ሥራው ላይ እናተኩራለን፡፡ ሦስተኛ፣ ስለ ጸጋ አስተዳደሩ እንነጋገራለን፡፡ አራተኛ፣ የሚሰጠውን ራዕይ እናብራራለን፡፡ በፈጣሪነት ኃይሉ እንጀምር፡፡

# የመፍጠር ኃይል

“የመፍጠር ኃይል” በሚለው ቃል ለማለት የፈለግነው፣ አዳዲስ ነገሮችን ለመፍጠር ያለውን ችሎታ እና የተፈጠረውን ለማስተዳደርና ለተፈጠረበት ዓላማ በአስፈላጊ ለውጥ ለማዘጋጀት ያለውን ችሎታ ነው፡፡

*የመጽሐፍ ቅዱስን የመጀመሪያ ገጽ ስንገልጥና ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ስንመለከት፣ መንፈስ በውኆች ላይ ሰፍፎ ነበር፣ ያም መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ወደ ቆላስያስ ምዕራፍ 1 ስትገልጡ ደግሞ፣ ክርስቶስ ፈጣሪ መሆኑንና በመንፈስ ቅዱስም አማካይነት የሚፈጥር መሆኑን ታነብባላችሁ፡፡ መንፈስ ደግሞም በዳግም መፈጠር ውስጥም ይሳተፋል፡፡ ዳግም መፈጠር የምንለው ከመለወጣችን አንፃር ያለውን ነው፡፡ ዳግም ልደትን የሚሰጥ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ሰው ከመንፈስ ካልተወለደ በስተቀር፣ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም፡፡ መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዳችን አዲስ ልደት በመስጠት ብቻ አያበቃም፣ ፍጥረተ-ዓለሙንም እንደገና ይፈጥራል፡፡ ስለዚህም ጳውሎስ በሮሜ 8 ፍጥረት ሁሉ የእንደገና በአዲስ የመፈጠርን ተሃድሶ በመቃተት የሚጠባበቅ መሆኑን ያም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሆኑን ገልጧል፡፡ [ዶ/ር ዴሪክ ደብሊዩ. ኤች. ቶማስ]*

ስለ መንፈስ ቅዱስ የመፍጠር ኃይል የምናደርገው ውይይት በሦስት የተለያዩ የሥራው እንቅስቃሴዎች ላይ ያተኩራል፡፡ በመጀመሪያ፣ በፍጥረታዊው ዓለም ውስጥ ስላለው የመፍጠር ሥራው እንነጋገራለን፡፡ ሁለተኛ፣ ለቤተክርስቲያን በሚሰጣቸው የጸጋ ስጦታዎች ላይ እናተኩራለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ በእኛ ሰብዓዊ መንፈስና ልብ ህዳሴ ላይ በሚሠራው ሥራ ላይ እናተኩራለን፡፡ በፍጥረታዊው ዓለም ላይ የእርሱ የመፍጠር ኃይል በሚገለጥበት መንገድ እንጀምራለን፡፡

## ፍጥረታዊ ዓለም

በፍጥረታዊው ዓለም ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን የመፍጠር ሥራ የምናገኘው በመጽሐፍ ቅዱሳችን የመክፈቻ ጥቅሶች ውስጥ ነው፡፡ ቀደም ብለን በዚህ ትምህርታችን፣ በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 በተገለጠው የፍጥረት ታሪክ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን ድርሻ ስንመለከት፣ ዓለምን ከምንም ነገር ውስጥ ለመፍጠር ከመለኮታዊ ሁሉን ቻይነቱ ያነሰ ነገር እንዳልተጠቀመ ተመልክተናል፡፡ ተመሳሳዩንም ሃሳብ በመዝሙር 104 ቁጥር 30 ላይ፣ በመጀመሪያው የመፍጠር ሳምንት ብቻ ሳይሆን ዕለት በዕለትም ምድርንና በውስጥዋ ያለውን ፍጥረት ሁሉ ለመፍጠር እግዚአብሔር መንፈሱን በመላኩ ሲያመሰግን እናገኛለን፡፡ መዝሙር 33 ቁጥር 6

ይህንኑ ሃሳብ ያስተጋባል፤ ኢዮብ 33 ቁጥር 4 ደግሞ በተለይም ከሰብዓዊ ፍጡር አንፃር ይህንን ሃሳብ በስፋት ያስቀምጠዋል፡፡

አንድ ምሳሌ ለመውሰድ፣ በመዝሙር 104 ቁጥር 30 የተጻፈውን አድምጡ፡-

> መንፈስህን ትልካለህ ይፈጠራሉም፥ የምድርንም ፊት ታድሳለህ። (መዝ 104፥30)

በዚህ ጥቅስ፣ በፍጥረት ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ነገር እንዴት ወደ መኖር እንደመጣ ዘማሪው ያለውን መረዳት ይገልፃል፡፡ ሁሉም ነገር በእግዚአብሔር መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ እንደተፈጠረም ይናገራል፡፡

የመንፈስ ቅዱስ የመፍጠር ኃይል በፍጥረተ ዓለሙ ውስጥ በቅዱሳት መጻሕፍት በገለፃቸው በርካታ ተዓምራትም ታይቷል፡፡ ለምሳሌ፣ በብሉይ ኪዳን በዘፀዓት ምዕራፍ 17 ቁጥር 6 ላይ ሙሴ ከዐለቱ ውሃ እንዲያገኝ በማስቻል፡፡ በ1ኛ ነገሥት ምዕራፍ 17 የመበለቲቱን ዱቄትና ዘይት በማብዛት ተገልጧል፡፡

በአዲስ ኪዳን፣ በማቴዎስ ምዕራፍ 14 አምስት ሺህ ሰዎችን እና በማቴዎስ ምዕራፍ 15 ደግሞ አራት ሺህ ሰዎችን እንዲመግብ የተገኘውን እንዲትረፈረፍ ኢየሱስን በማስቻል፡፡ ሮሜ ምዕራፍ 8 ቁጥር 11 ስናነብብ ኢየሱስን ከሞት በማስነሣት ተገልጧል፡፡ ከሮሜ ምዕራፍ 15 ቁጥር 18 እና 19 እንደምንማረው የጳውሎስን አገልግሎትና በአገልግሎቱ የተገለጡ ተዓምራት እንዲከናወኑ በማስቻል ኃይል ተገልጧል፡፡

እርግጥ ነው፣ ከተዓምራት ሁሉ የላቀው ተዓምራት ትስጉት ነው፣ ያም ድንግሊቱ ማርያም ኢየሱስን እንደትትፀንስ ማድረጉ ነው፡፡ ይህ ልዩ ተዓምራት፣ በሉቃስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 35 የተመዘገበ ሲሆን፣ በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንደሆነ ተለይቶ ተገልጧል፡፡

ዛሬም ቢሆን፣ መንፈስ ቅዱስ የመፍጠር፣ የማደስ እና ፍጥረተ ዓለሙ ሁሉ እግዚአብሔር ያቀደለትን ሆኖ እንዲገኝ የማድረግ አስገራሚ ኃይል አለው፡፡

እንደ እውነቱ፣ የሰው ዘር በኀጢአት ምክንያት ያለበትን የውድቀተ ዓለም ገፅታ ሙሉ በሙሉ እስከሚቀይር ድረስ ዓለምን የማደስ ሥራው አያቆምም፡፡ ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 እንደሚነግረን፣ አዳምና ሔዋን መልካምንና ክፉን ከምታስታውቀው ዛፍ በበሉ ወቅት እግዚአብሔር ረግሟቸዋል፡፡ የሰው ዘር የእግዚአብሔር ወኪል ሆኖ ምድርን ሁሉ እንዲገዛ ሥልጣን

ተሰጥቶት ስለነበረ፣ በአዳምና በሔዋን ላይ ያረፈው የእግዚአብሔር እርግማን ፍጥረትን ሁሉ ፣ ምድሪቷን አንኳን ሳይቀር ተፅዕኖ አሳድሮባታል፡፡

ከዚያን ጊዜ አንስቶ፣ መንፈስ ቅዱስ ዓለምን ለማደስና ወደ ፍፃሜው ለማምጣት በሥራ ላይ ይገኛል፡፡ ውጤቱም ኢሳያስ ምዕራፍ 65 ቁር 17 እና ምዕራፍ 66 ቁጥር 22፤ 2ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 3 ቁር 13 እና ራዕይ ምዕራፍ 21 ቁር 1 የመሳሰሉትን ስናነብብ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደሆነ እንረዳለን፡፡

በፍጥረተ ዓለሙ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን የመፍጠር ኃይል ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ለቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ስጦታዎችን በመስጠት የእርሱን የመፍጠር ኃይል እንዴት እንደሚጠቀምበት እንመለከታለን፡፡

## የፀጋ ሥጦታዎች

ስለ ፀጋ ስጦታዎች ስንነጋገር በልቡናችን የምናሰላስለው፡

ቤተክርስቲያንን ለማነፅ መንፈስ ቅዱስ ለሰዎች የሚሰጣቸውን ምንጫቸው መለኮት የሆነውን ችሎታዎች ነው፡፡

መንፈስ እነዚህን ስጦታዎች የሚገልጠው ቀድመው ያጡዋቸውን አዳዲስ ክህሎቶችን በሰው ውስጥ በማፍለቅ ወይንም በተቀባዩ ውስጥ የነበሩትን ክህሎቶች ወይም ልምምዶች ከተፈጥሮአዊው ድንበር ባሻገር እንዲገለጡ በማስቻል ነው፡፡

*በአዲስ ኪዳን የሚገለጡ የጸጋ ስጦታዎች ልዩ፣ ከልዕለ ተፈጥሮ የሚሰጡ ድንቅ ችሎታዎች ናቸው፡፡ ከሰብዓዎዊ ተሰጥዖ እጅግ የሚልቁ በመሆናቸው ላይ አፅንዖት መስጠቱ አስፈላጊ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ለአማኝ ሁሉ ከልዕለ ተፈጥሮ የሚሰጡ ናቸው፡፡ እያንዳንዱ አማኝ የጸጋ ስጦታ እንዲያውም ስጦታዎች ሊኖሩት ይችላል፡፡ [ዶ/ር ማርክ ስትራውስ]*

ለቀደምቷ ቤተክርስቲያን ተሰጥተው የነበሩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ዝርዝርና ዓይነት ሮሜ ምዕራፍ 12፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 12 እና ኤፌሶን ምዕራፍ 4 የመሳሰሉ ስፍራዎች ላይ ተጠቅሰዋል፡፡ ከእነዚህ ስጦታዎች አንዳንዶቹ ከተፈጥሮ ስጦታዎች ወይንም ዓለም አቀፋዊ ሰብዓዊ ተሰጥዖዎች ጋር ይመሳሰላሉ፡፡ እነርሱም ከቤተክርስቲያን ውጪ ባሉ ሰዎችም ውስጥ እንኳን በተወሰነ መጠን ይሠራሉ፣ ምክንያቱም በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ በመሆናቸው ነው፡፡ ብንጠቅሳቸውም፣ ጥበብ፣ እውቀት፣ ማገልገል፣ ማስተማር፣ ማበረታታት፣ ቸርነት፣ መሪነት እና ምህረት የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ግን ሌሎቹ ሥጦታዎች እንደ ፈውስ እና ተዓምራዊ ኃይል

የሚገለጥባቸው መለኮታዊ ምንጭ ያላቸው መሆኑ በግልፅ ይታወቃል፡፡ የተቀሩት ደግሞ በተፈጥሮአዊውና በልዕለ ተፈጥሮአዊው መካከል የሚንጠለጠሉ ለምሳሌ እንደ ትንቢት፣ በልሳን መናገር፣ ልሳንን መተርጎም እና የመለየት ስጦታዎች ይኖራሉ፡፡

ሁሉም ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ ስጦታዎችን እንደሚሰጥ ይስማሙበታል፡፡ በዚህ ጥቅል ስምምነት ውስጥ ግን፣ በሰጡዋቸው ደረጃዎች መሃል የሚወድቁ የተለያዩ በግልፅ የሚንፀባረቁ አመለካከቶች አሉ፡፡ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ተቋርጧል የሚል አቋም በመያዝ፣ በዘመነኛው ዓለም መንፈስ ቅዱስ ከተፈጥሮ ስጦታ ጋር የሚመሳሰሉ ስጦታዎችን ብቻ ይሰጣል፡፡ ምናልባትም ከሐዋርያት ዘመን በኋላ ወይንም ከቅዱሳት መጻሕፍት ካኖን በኋላ ሌሎቹ ዕፁብ ድንቅ ስጦታዎች ጠፍተዋል ብለው ያምናሉ፡፡

ሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ፣ መንፈስ ቅዱስ ዛሬም በአዲስ ኪዳን ተገልጠው የምናገኛቸውን ሥጦታዎች ይሰጣል የሚለውን አቋም ይይዛሉ፡፡ በዚህም አቋም ውስጥ፣ እያንዳንዱ ክርስቲያን እቀበላለሁ ብሎ ሊጠብቃቸው የሚገቡ የትኞቹ ናቸው? በሚለው ላይ የተለያዩ አመለካከቶች አሉ፡፡

በነዚህ ሁለት ፅንፎች መካከል፣ በርካታ ሚዛናቸውን የጠበቁ አመለካከቶችም አሉ፡፡ ሚዛናቸውን የጠበቁ አብያተ ክርስቲያናት መንፈስ ቅዱስ አሁንም እርሱ በወደደ ጊዜ አስደናቂዎቹን ስጦታዎች ይሰጣል ብለው ያምናሉ፡፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ለቤተክርስቲያን ሁሉንም ስጦታዎች ሊሰጥ ይገባል በማለት ሊያስገድዱት አይሞክሩም፡፡ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት መንፈስ ቅዱስ በወደደው ጊዜና ዓይነት እንዲሠራ ነፃነትን ይሰጡታል፡፡

ሁለቱም አቋሞች የጋራቸው የሆነው እምነት መንፈስ ቅዱስ አሁንም ለቤተክርስቲያኑ ጥቅም ቢያንስ ቢያንስ የተወሰኑ ስጦታዎችን ይሰጣል የሚለው ነው፡፡ መንፈሳዊ ስጦታዎች የእግዚአብሔር ኃይል ናቸው፣ አገልግሎት ላይ ሊውሉ የሚገባውም ለእርሱ ሕዝብ በጠቅላላ ነው፡፡ ቤተክርስቲያንን ለአገልግሎት ለማዘጋጀትና ወደ ክርስቶስ ለማደግ ይሰጣሉ እንጂ የሰዎችን ሰብዓዊ ፍላጎት ለማርካት እንዲያውም የግለሰቦችን መንፈሳዊ ሕይወት ልዩ ለማድረግ አይሰጡም፡፡ ይህንንም በሮሜ ምዕራፍ 12 ቁጥር 4 እና 5፤ 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12 ቁጥር 7 እና ኤፌሶን ምዕራፍ 4 ከቁር 7 እስከ 16 ላይ እንመለከታለን፡፡ አንዱን ለምሳሌ ለማንሳት ያህል፣ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12 ቁር 7 የፃፈውን አድምጡ፡

> ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል። (1ቆሮ 12፥7)

ጳውሎስ በዚህ ስፍራ እንዳመለከተው፣ መንፈሳዊ ስጦታዎች የሚሰጡት ለቤተክርስቲያን ጥቅም ነው፡፡ ስጦታው የተሰጣቸውም ሰዎች ምናልባት ከስጦታቸው ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የስጦታዎቹ ተቀዳሚ ግብና ትኩረት ግን የቤተክርስቲያን ጥቅም ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያንን በጠቅላላ ለማነፅ የሚጠቀምባቸው የአርሱው ኃይል መገለጫዎች ናቸው፡፡

*ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች ልናውቀው የሚገባ እጅግ አስፈላጊ ነገር ማደግ የሚገባቸው፣ በቤተክርስቲያን ማለትም በክርስቶስ አካል ውስጥ ሊለዩና አገልግሎት ሊሰጥባቸው የተገባ መሆኑ ነው፡፡ መንፈሳዊ ስጦታዎች ለግለሰቦች ብቻ የተሰጡና በግሉ እንደወደደ የሚገለገልባቸውና ራሱ ብቻ የሚጠቀምባቸው አይደሉም፡፡ በርካታ ሰዎችን፣ አማኞችን፣ በተለይም የኢየሱስ ክርስቶስን ቤተክርስቲያን ለማነፅ የሚሰጡ ናቸው፡፡ [ዶ/ር ሬይድ ካሲስ፣ ትርጉም]*

*መንፈሳዊ ስጦታዎች ቤተክርስቲያንን ለማነፅ፣ ቤተክርስቲያንን ለመገንባት፣ ክርስቲያናዊ አገልግሎትን ለመስጠት፣ እርስ በርስ ለመበረታታትና ታላቁን ተልዕኮ ለማሳካት ከመንፈሱ ለእኛ የተሰጡ ናቸው፡፡ በእኛ ዘመን ተቀዳሚ ትኩረት የምንሰጠው፣ በተለይም በልሳን መናገርን አስመልክቶ ባለው ካሪዝማዊ ጉዳይ እና ትንቢት በቅዱሳት መጻሕፍት ግን ሁለተኛ ትኩረት የተሰጠው ሆኖ እናያለን፡፡ በመንፈሳዊ ስጦታዎች ላይ ማትኮር የሚገባን አዲስ ኪዳን በሚያተኩርበት ዓይነት ነው፡፡ የሚያጽናናን መሆኑን፣ የአዲሱ ኪዳን ዘመን ንጋት ወገግ ያለ መሆኑን፣ የመንፈሱ ሥራ በውስጣችን በግል እና በእርሱ ህዝብ ውስጥ በጋራ እየተፈፀመ መሆኑን፣ በዚህም ምክንያት ለዓለም አገልግሎት የሚሰጥበት አቅም በግል እና በጋራ መገኘቱን እንረዳለን፡፡ በዚህም ወቅት አፅንዖት የምንሰጠውና ልናተኩርበት የሚገባ ነገር በዓለም በምንኖርበት በግል ሕይወታችን አልፎም በአንድነት የቤተክርስቲያን ሕይወታችን እርሱ የሚሠራውን ሥራ ነው፡፡ [ዶ/ር ስቴፈን ዌሉም]*

መንፈስ ቅዱስ በፍጥረታዊው ዓለም ውስጥ የእርሱን የመፍጠር ኃይል እንዴት እንደሚጠቀምበትና ለቤተክርስቲያን የሚሰጠውን ስጦታ ግንዛቤ ይዘን፣ ይኸው ኃይል በእያንዳንዱ አማኝ መንፈስና ልብ ውስጥ እንዴት እንደሚገለጥ እንመልከት፡፡

## ግላዊ ኀዳሴ

ሰዎች መንፈሳዊ ሞትን ይዘው እንደሚወለዱ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምሩናል፡፡ እንደ ሮሜ ምዕራፍ 5 ከቁጥር 12 እስከ 19 በአዳም በደል ምክንያት በደለኞች ነን፣ በውጤቱም ለሞት የተሰጠን ሆንን፡፡ ስለዚህ፣ እኛን ከዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ለማዳን መንፈስ ቅዱስ መንፈሳችንን በእግዚአብሔር ፊት ሕያዋን ለማድረግ አዲስን ሕይወት በውስጣችን ሊፈጥር አስፈልጎታል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ አዲስ ሕይወት ከዳግም ልደትና ከመታደስ አንፃር ይናገራል፡፡ ስለዚህ ደግም መወለድ በዮሐንስ ምዕራፍ 3 ከቁር 3 እስከ 8፤ ቲቶ ምዕራፍ 3 ቁጥር 5፤ 1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 5 ከቁር 1 እስከ 18 እና በሌሎችም በርካታ ቦታዎች እናነባለን፡፡ ለምሳሌ ያህል፣ በቲቶ ምዕራፍ 3 ቁጥር 5 ጳውሎስ የተናገረውን አድምጡ፡

> እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፥... (ቲቶ 3፥5)

ዳግም ከተወለድን በኋላ፣ መንፈስ ቅዱስ አስተሳሰባችንን፣ ስሜታችንን እና ተግባራችንን በመለወጥ ጌታን የሚወድዱና የሚታዘዙ ሕዝቦች ለማድረግ በእኛ ውስጥ ሥራውን ቀጥሏል፡፡ አዲስ ኪዳን ስለዚህ ነገር ሮሜ ምዕራፍ 8 ከቁጥር 1 እስከ 16፤ 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12 ቁጥር 3፤ ገላትያ ምዕራፍ 5 ከቁጥር 16 እስከ 25 እና ፊልጵስዩስ ምዕራፍ 2 ቁር 13 ላይ ይናገራል፡፡ የመንፈስ ቅዱስን የመለወጥ ኃይል አስመልክቶ እውቅ የሆነው ቃል ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ሕይወት ውስጥ ስለሚያፈራው ፍሬ የገለጠበት ነው፡፡ እስኪ ጳውሎስ በገላትያ ምዕራፍ 5 ቁጥር 22 እና 23 ላይ የፃፈውን አድምጡ፡

> የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው። (ገላ 5፥22-23)

እነዚህ ለውጦች በባሕርያችን ውስጥ ሊታዩ የሚችሉት መንፈስ ቅዱስ እኛ ክርስቶስን እንድንመስል ለማድረግ በውስጣችን ከሚሠራው ንቁና የመፍጠር ኃይል ጋር ነው፡፡

በመጨረሻውም ቀን፣ መንፈስ ቅዱስ በእምነት የፀኑ ክርስቲያኖችን አካል በመፍጠር ጉልበቱ በማስነሣት፣ ፍፁምና የማይሞተው የክርስቶስ አካል እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ በሮሜ ምዕራፍ 8 ቁጥር 23 ጳውሎ ስለዚህ ነገር የተናገረውን አድምጡ፡

> እርሱም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን የመንፈስ በኵራት ያለን ራሳችን ደግሞ የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነት እየተጠባበቅን ራሳችን በውስጣችን እንቃትታለን። (ሮሜ 8፥23)

ጳውሎስ የክርስቶስ ተከታዮች የመንፈስ በኩራት አላቸው ሲል፣ ቋንቋውን የወሰደው በብሉይ ኪዳን የዓመቱን ሁሉ መከር በመወከል ስለሚቀርበው የመከር የበኩራት መስዋዕት ልምምድ ከሚነገረው ቃል ነው፡፡ ልክ እንደዚሁ፣ እንዲያውም በበለጠ፣ መንፈስ ቅዱስ አሁን በአማኞች ሕይወት ውስጥ የሚሠራውም ሥራ ወደፊት ለሚመጣው የበለጠ ሥራ በኩር ነው ማለት ነው፡፡ እኛን ፍፁም አዲስ አድርጎ እስኪሠራን፣ እርግማናችንንና ርኩሰታችንን እስኪያስወግድ፣

ወደ ቀደመው ንፁህና እና ኃጢአት አልባ ወደ ሆነው ማንነታችን እስኪመልሰን ድረስ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ አያበቃም፡፡ በመሠረቱ መንፈስ ለመንፈሳችን አዲስን ሕይወት ሰጥቶናል፡፡ በመጨረሻውም አካላችንን እንደገና ይፈጥራል፡፡

የመንፈስ ቅዱስን የመፍጠር ኃይል ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ወደ መቀደስ ሥራው ትኩረታችንን እናዞራለን፡፡

# ቅድስና

ስለ መንፈስ ቅዱስ የመቀደስ ሥራ ስንነጋገር፣ ሰዎችንና ነገሮችን ስለ መቀደስ ተግባሩ መናገራችን ነው፡፡ ይህም ሰዎችንና ነገሮችን ለእግዚአብሔር የተለዩ ለማድረግ፣ ለማንፃት እና ወደ ማይሸፈነው ክብሩ ለማቅረብ መንፈስ የሚሠራውን ሥራ የሚያመለክት ነው፡፡ ይህም በብዙ መንገድ፣ በዚህ ትምህርት መጨረሻ ላይ ከምንመለከተው የተሃድሶ ጽንሰ-ሃሳብ ጋር የሚዛመድ ሃሳብ ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ቤተክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ኅላዌና አገልግሎት የተቀደሰችና ንፁህ ናት በማለት ይናገራል፡፡ ይህንንም ሃሳብ ሮሜ ምዕራፍ 15 ቁጥር 16፤ 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 6 ቁጥር 11፤ 2ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ 2 ቁጥር 13 እና 1ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 1 ቁር 1 እና 2 ላይ እናገኛለን፡፡ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 16 እና 17 ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚናገርበትን መንገድ አድምጡ፡

> የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን?
> ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፥ ያውም እናንተ ናችሁ። (1ቆሮ 3፥16-17)

በብሉይ ኪዳን፣ የአይሁድ መቅደስ የእግዚአብሔር ልዩ መገኘት ያለበት ምድራዊ ስፍራ ነበር፡፡ ሰለሞን በ2ኛ ዜና ምዕራፍ 6 ቁጥር 1 እንዳወጀው በምድር ያለ ቤቱ እንደ ማለት ነው፡፡ በአዲስ ኪዳን ግን፣ እግዚአብሔር በመቅደስ ውስጥ አይኖርም፡፡ በምትኩ ግን፣ መንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያንን አዲሲቷ መቅደስ አድርጎ ቀድሷታል፡፡ ይኸው ተመሳሳይ ሃሳብ ተለይቶ በኤፌሶን ምዕራፍ 2 ቁጥር 22 ላይ ተገልጧል፣ በሌሎችም የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች ውስጥ ተስተጋብቷል፡፡

መንፈስ ቅዱስ በተጨማሪም በክርስቲያኖች ውስጥ በማደር ይቀድሳቸዋል ተብሎም ተነግሯል፡፡ ይህም ሃሳብ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ልብ ውስጥ ይኖራል ማለት ነው፡፡ ይህ

በአማኞች ውስጥ የማደሩ ሃሳብ በበርካታ ስፍራዎች ተጠቅሷል፣ ለምሳሌ፣ ሮሜ ምዕራፍ 8 ከቁጥር 9 እስከ 16፤ 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 6 ቁጥር 19፤ 2ኛ ጢሞ ምዕራፍ 1 ቁጥር 14 እና ያዕቆብ ምዕራፍ 4 ቁጥር 5፡፡

*የመንፈስ ቅዱስ በአማኝ ውስጥ የማደሩ ጉዳይ ለአማኝ እጅግ ወሳኝ እውነታ ነው፡፡ እግዚአብሔር በውስጣቸው ሲገባ እና ክርስቲያኖችን በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ሲያደርጋቸው፣ መንፈስ ቅዱስ ሕይወታቸውን ይረከባል፡፡ ስለዚህ በእርሱ መደገፋችን፣ በውስጣችን ባደረው ኃይሉ መታመናችን እጅግ ወሳኝ ነው፣ ያለበለዚያ ግን እንዲያው በሥጋ መኖር ብቻ ይሆናል፡፡ በመንፈስ እና በሥጋ የመኖርን ልዩነት መናገር መቻል ይኖርብናል ምክንያቱም በመንፈስ መኖር ክርስቶስን ለማክበርና እርሱ እንድንሆንለት በሚፈልገው መንገድ መኖር የሚያስችለን ነውና፡፡ [ዶ/ር ኤሪክ ኬ. ቶኔስ]*

ይህ የመንፈስ ቅዱስ በአማኝ ውስጥ ማደር በርካታ ውጤቶች አሉት፡፡ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ፣ ከኃጢአት ያነፃናል፣ ለእግዚአብሔር ይለየናል፣ በልባችንና በአዕምሯችን መንፈስ ቅዱስ በሚያሳድረው ተፅዕኖ እናተርፋለን ደስም እንሰኛለን፡፡ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 6 ከቁጥር 9 እስከ 11 ስለዚህ ጉዳይ እንዴት እንደሚገልፅ አድምጡ፡

ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ፤ ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀራጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ
ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደ እነዚህ ነበራችሁ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፥ ተቀድሳችኋል፥ ጸድቃችኋል። (1ቆሮንቶስ 6፥9-11)

በመንፈስ ቅዱስ የመቀደስ ሥራ፣ አማኞች ነፅተው ለእግዚአብሔር ተለይተዋል፣ ስለዚህም ከአመፀኞች ጋር ፈፅሞ አይቆጠሩም፡፡

እግዚአብሔር ራሱ በውስጣችሁ የመኖሩ ነገር እጅግ ልዩ ስለ መሆኑ ማሰብ አቁማችሁ ታውቃላችሁ? የፍጥረተ ዓለሙ ፈጣሪ እናንተን እጅግ ከመውደዱ የተነሳ ለዘላለም እናንተን ከራሱ ጋር አንድ አድርጓል፡፡ እናንተ በእርሱ የማረጋገጫ የግርጌ ማህተም ላይ አይደላችሁም፡፡ በልቡ ውስጥ ተሰውራችኋል፡፡ ይህም ግንኙነት በኃጢአት ላይ ብርቱ ያደርጋችኋል፡፡ ፈተናን የምትቋቋሙበትንም ኃይል ይሰጣችኋል ደግሞም እግዚአብሔርን ደስ በማሰኘት እንድትኖሩ

ያስችላችኋል፡፡ ኃጢአት ስትሠሩ፣ ምንም ያህል የከፋ ቢሆንም እንኳን በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ያላችሁ ናችሁ፡፡ ወደ እርሱ ፊት ለመቅረብና ከእርሱ ጋር ኅብረት ለማድረግ፣ ለማምለክ እንዲያውም የእርሱን ይቅርታ ለመጠየቅና ለመቀበል ትችላላችሁ፡፡

የመንፈስ ቅዱስን የመፍጠር ኃይልና የመቀደስ ሥራውን ተመልክተናል፡፡ አሁን ደግሞ፣ መለኮታዊ ጸጋውን ስለ ሚያስተዳድርባቸው በርካታ መንገዶች ለመነጋገር ዝግጁ ነን፡፡

# ጸጋ

ስለ መንፈስ ቅዱስ ሦስተ የጸጋ አስተዳደር ዓነቶች እንነጋገራለን እነርሱም የወል ጸጋ፣ የቃል ኪዳን ጸጋ እና የድነት ጸጋ ናቸው፡፡

## የወል ጸጋ

የወል ጸጋ እግዚአብሔር ምንም ይሙኑ ምን ለሰው ዘር በጠቅላላ የሚያሳየውን የዚህንም ትሩፋት የሚቀበሉበትን መግቦት የሚመለከት ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ የወለል ስጦታዎችን ለሁሉም ህዝብ እኩል አይሰጥም፡፡ በምትኩ ግን እርሱው እንደወደደና በዕቅዱ መሠረት እዚህና እዚያ ይሠራል፡፡

ለምሳሌ፣ የወል ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ኃጢአት በዓለም ላይ ያለ ልክ እንዳይሰለጥን በመከልከል ይገለጣል፡፡ ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ 8 ከቁጥር 1 እስከ 8 እንዳስተማረው የወደቁት የማያምኑ ሰዎች በኃጢአት ቁጥጥር ውስጥ ናቸው፡፡ ከፍጥረታቸው በእግዚአብሔር ላይ አመፀኞች ናቸው ኃጢአት ማድረግንም ይወድዳሉ፡፡ ጳውሎስ በሮሜ ምእራፍ 7 እና 8 እንዳስተማረው ግን፣ መንፈስ ቅዱስ በዓለም ላይ የሚሠራውን ኃጢአት ይዋጋል፡፡ ይህም አዳዲስ አማኞችን እንደገና ከወለዳቸው በኋላ ከሚሠራበት መንገድ ጋር ይመሳሰላል፡፡ ምንም እንኳን ለማያምኑት የላቀ በረከት ባያስገኝላቸውም፣ ሊያደርጉ የሚችሉትን ያህል ኃጢአት እንዳይሠሩ ግን ይከለክላቸዋል፡፡

በዓለም ላይ በስፋት የሚታየው የወል ጸጋ ሌላው ገፅታ የማያምኑት የሚያገኙት እውቀት እና በዚያም እውቀት የሚያከናውኑት በጎ ተግባር ነው፡፡ የማያምኑ ሰዎች ቤተክርስቲያንና አማኞቿን፣ ከተቀረው ማህበረሰብ ጋር የሚጠቅሙባቸውን በርካታ ተግባራትን የሚያከናውኑባቸውን እውነታዎች ያውቃሉ፡፡ አንድ ሰው ማንኛውንም ጠቀሜታ ያለው ነገር ካገኘ፣ ያ እውቀት የመንፈስ ቅዱስ በጎ ስጦታ ነው፡፡

ከ1509 እስከ 1564 ዓ.ም. የኖረው የፕሮቴስታንት ተሃድሶ አራማጅ ጆን ካልቪን Institutes of the Christian Religion በተሰኘው *ሥራው* 2ኛ መጽሐፍ ምዕራፍ 2 ክፍል 15 እና 16

ላይ የመንፈስ ቅዱስን የእውቀት የወል ስጦታዎች አብራርቷል፡፡ በዚያ ከጻፈው ጥቂቱን አድምጡ፡

*እነዚህን ጉዳዮች በዓለማውያን ጸሐፊዎች ሥራ ውስጥ ስናገኝ፣ ያ በእነርሱ ውስጥ የተገለጠ አስደናቂ የእውነት ብርሃን፣ የሰው ልቡና፣ ምንም እንኳን የወደቀ እና ከምልዐቱ የጎደለ ቢሆንም፣ በእግዚአብሔር ግሩም ስጦታ የተዋበ መሆኑን ያስተምረናል፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ የእውነት ሁሉ ብቸኛ ምንጭ ነው ካልን፣ አንድም እውነቱን እናቃልላለን፣ አሊያም በተገለጠበት ስፍራ ሁሉ እናቃልለዋለን፣ ይህንንም ልናደርግ የምንችለው የእግዚአብሔርን መንፈስ ከበሬታ ለመንሳት ስንፈልግ ብቻ ነው… ጌታ ግን የማያምኑ ሰዎች በሚያከናውኗቸው ተግባራት በፊዚክስ፣ ዳይሌክቲክስ፣ በሂሳብ እና በተመሳሳይ እውቀቶች እንድንታገዝ ከወደደ፣ እገዛቸውን ልንጠቀምበት ይገባል፡፡ [ጆን ካልቪን]*

# የቃልኪዳን ጸጋ

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በበርካታ ስፍራ፣ በመንፈስ ቅዱስ የሚመራውን ሁለተኛውን ጸጋ እንመለከታለን ያም አንዳንድ ጊዜ የቃልኪዳን ጸጋ ተብሎ ይጠራል፡፡

የቃልኪዳን ጸጋ እግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ህዝብ፣ ምንም እንኳን እውነተኛ አማኞች ባይሆኑም የሚሰጠውን ስጦታ የሚያካትቱ ቸርነቶችን ያካተተ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን፣ እግዚአብሔር ለአብርሃም፣ ለሙሴና ለዳዊት በገባው ልዩ ኪዳን ምክንያት የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ህዝብ የምትታየዋ ቤተክርስቲያን ስትሆን እርሷም ምንም እንኳን እውነተኛ አማኞች ባይሆኑም ከእርሷ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሁሉ ያካተተች ናት፡፡ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ጸጋ ከወል ጸጋ ይልቅ የተትረፈረፈና በርካታ ነገሮችን የያዘ ነው፡፡

ለምሳሌ፣ የቀደመችው እስራኤል ምንም እንኳን በተደጋጋሚ ያልታመነች ብትሆንና በእርሱም ላይ አብዝታ ኃጢአትን ብትሠራም እግዚአብሔር ግን ታጋሽና ምህረትን የተሞላ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር በገባው ቃል ኪዳን ምክንያት፣ እንደ መንግሥት ደብዛቸውን አላጠፋም፣ ግን ዘወትር የታመኑ ቅሬታዎችን ያስቀር ነበር፡፡ በሮሜ ምዕራፍ 11 ከቁጥር 1 እስከ 5 ጳውሎስ ስለዚህ ነገር በግልጽ ይናገራል፡፡ በተጨማሪም፣ ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የተነሣ፣ በጥንታዊቷ እስራኤል የሚኖሩ የማያምኑትም እንኳን የእርሱን በረከት ተቀብለዋል፡፡ የዚህ ነገር ትልቁ ምሳሌ ከግብፅ ነፃ መውጣታቸው ነው፡፡ በዘፀአት ምዕራፍ 2 ከቁጥር 23 እስከ 25 ሙሴ የጻፈውን አድምጡ፡

ከዚያም ከብዙ ቀን በኋላ እንዲህ ሆነ የግብፅ ንጉሥ ሞተ የእስራኤልም

ልጆች ከባርነት የተነሣ አለቀሱ፥ ጮኹም፥ ስለ ባርነታቸውም
ጩኸታቸው ወደ እግዚአብሔር ወጣ።
እግዚአብሔርም የለቅሶአቸውን ድምፅ ሰማ፥ እግዚአብሔርም
ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን አሰበ።
እግዚአብሔርም የእስራኤልን ልጆች አየ፥ እግዚአብሔርም በእነርሱ
ያለውን ነገር አወቀ። (ዘፀ 2፥23-25)

እግዚአብሔር ስለእስራኤል ለምን ግድ እንዳለውና ነፃ እንዳወጣቸው አስተውሉ፡፡ ለእርሱ ታማኝ ስለነበሩ ሳይሆን፣ ከአባቶቻቸው ከአብርሃም፣ ከይስሐቅና ከያዕቆብ ጋር በገባው ቃል ኪዳን ውስጥ ስለተካተቱ ነበር፡፡

አሁንም በቤተክርስቲያን ነገሩ እውነት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ የቤተክርስቲያን አካል የሆነ የትኛውም ሰው ዘወትር የወንጌልን መልእክት የመስማት እና ንስሓ በመግባት የመዳን እድል ያገኛል፡፡ ከዕብራውያን ምዕራፍ 6 ከቁጥር 4 እስከ 6 እንደምንማረው፣ እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን የሰጣቸውን እነዚህን ስጦታዎች እነርሱም ይካፈላሉ፡፡ ዕብራውያን ምዕራፍ 10 ቁጥር 29 በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ አማኞች ባለማመናቸው ምክንያት የጸጋውን መንፈስ ያከፋፉሉ ብሎ የሚናገረው በዚህ ምክንያት ነው፡፡

*በቤተክርስቲያን ውስጥ ስንካፈል፣ የዳኑና ያልዳኑ ሰዎችን እናገኛለን፡፡ በክርስቲያኖች መገኘት ውስጥ ከመገኘታቸው የተነሳ ብቻ ያልዳኑ ሰዎች የሚያገኙት ጥቅም አለ፡፡ ያም መልካም ነገር ነው፡፡ እግዚአብሔር በዚህ የሚሠራውን ሥራ፣ ዘወትር እንዲህ ነው ብለን መናገር አንችልም፡፡ በዚያ መሆን ግን መልካም ነገር ነው፡፡ ጆን ካልቪን ስለ ወል ጸጋ ተናግረዋል፤ጆን ዌስሊ ደግሞ፣ ስለ እግዚአብሔር ቅድመ ድነት ጸጋ ተናግረዋል፡፡ ያም አንድ ሰው በይፋ በክርስቶስ ማመኑን ከማስታወቁ በፊት ጸጋ በሕይወቱ የሚሠራውን ሥራ የሚያመለክት ነው፡፡ ስለዚህም ያ ጸጋ እኔ እንደማስበው በሁለት ዋና መንገዶች በሥራ ላይ ነው፡፡ አንዱ፣ በኃጢአታችን መወቀሳችን ነው፡፡ ኃጢአት ጭብጥ መሆኑን፣ ኃጢአት አውዳሚያችን መሆኑንና የእግዚአብሔርንም ልብ እንደሚሰብር ማየት እንጀምራለን፡፡ ያንን ለማየት በጸጋ ስፍራ ውስጥ መሆን ይገባል፡፡ ከዚያም ያ የኃጢአት ወቀሳ በውስጣችን መሥራት ይጀምራል፣ ስለዚህም መበደላችንን እናምናለን፣ አንዳንድ የነገረ መለኮት ሰዎች እንደሚያስቀምጡትም ልንኖርበት የሚገባ ሌላ ሕይወት እንዳለ፣ የተሻለ ሕይወት እንዳለ ያመለክተናል፡፡ በተለይም ላልዳነ ሰው እንደምገምተው፣ ሕይወትን በዚህ ምቹ ስፍራ ተቀምጦ የሚያይበትን ዕድል ይሰጠዋል፣ ይህንንም ሲደርጉ እግዚአብሔር በሕይወታቸው መሥራት ይጀምራል፡፡ [ዶ/ር ስቲቭ ሃርፐር]*

*በእውነት በእግዚአብሔር መግቦት ወንጌልን በሚሰሙበት አውድ ውስጥ ይቀመጣሉ፣ በዚያም የተኖረውን ወንጌል ይመለከታሉ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ማን እንደሆነ፣ በቅዱሳንም ኅብረት ሕያው ሆኖ እንደሚገለጥና የመሳሰሉትን ይመለከታሉ፡፡ እናም፣ በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት፣ ከመዳናቸው በፊት እና አዲስ ሕይወት በማግኘት በቤተክርስቲያን ከመቀላቀላቸው በፊት ይህንን የመሰለ ለወንጌል ምላሽ እንዲሰጡ የሚያስችላቸውን ሥራ ይሠራል፡፡ [ዶ/ር ስቲቭ ባላከሞር]*

# የድነት ጸጋ

በመጨረሻም፣ ሦስተኛው የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ አስተዳደር ብዙ የነገረ-መለኮት ምሁራን የድነት ጸጋ ብለው የሚጠሩት ነው፡፡

የድነት ጸጋ በክርስቶስ እንከን የለሽ ሕይወት፣ ሞት፣ ትንሣኤ፣ ዕርገትና በክብር የመመለስ ዘላለማዊ በረከት እርሱን ጌታና አዳኝ አድርገው ለተቀበሉ የመገለጡ ማረጋገጫ ነው፡፡ እያንዳንዱ አማኝ ከመንፈስ ቅዱስ የሚያድነውን ጸጋ ይቀበላል፡፡

በመንፈስ ቅዱስ የድነት ጸጋ አስተዳደር የምንቀበላቸው በረከቶች በኢየሱስ ሥራ ምክንያት ለእኛ ተጠብቀውልናል፡፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ተግባራዊ እስካላደረጋቸው ድረስ በረከቶቹን አንቀበልም፡፡ ከእነዚህም በረከቶች መካከል በጣም ግልፅ የሆኑት ዳግም ልደት፣ መንፈስ ቅዱስ አዲስን ሕይወት ለመንፈሳችን የሚሰጥበት ነው፣ ከዚህም የተነሳ እኛ ዳግመኛ እንወለዳለን፡፡ ስለዚህም ነገር በዮሐንስ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 5 እስከ 8፣ ሮሜ ምዕራፍ 8 ከቁጥር 2 እስከ 11 እና ቲቶ ምዕራፍ 3 ቁጥር 5 ላይ እናነባለን፡፡ ሌላኛው ንስሓ ሲሆን፣ ይህም የኃጢአት ስርየት እና መጽደቃችን መንፈስ ቅዱስ የሚሠራቸው የማዳን ጸጋ ሥራዎች መሆናቸውን በዘካርያስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 10፤ 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 6 ቁጥር 11 እና ቲቶ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 5 እስከ 8 እንረዳለን፡፡ አዲስ ኪዳን በተጨማሪም ድነት በመንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን የሚገለጥ ምሉዕ ማንነት መሆኑን በ2ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ 2 ቁጥር 13 እና ቲቶ ምዕራፍ 3 ቁጥር 5 ላይ ይነግረናል፡፡

ክርስቲያኖች ስለ ግለሰባዊ ድነት ስንነጋገር፣ በኢየሱስ ክርስቶስና በሥራው ላይ ወደ ማትኮሩ እናጋድላለን፡፡ በመሠረቱ ይህ ልናደርገው የሚገባ ግሩም ተግባር ነው፡፡ ግን የመንፈስ ቅዱስንም ድርሻ ዋጋ መስጠቱ አስፈላጊ ነው፡፡

*መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ሕይወት ውስጥ የሚሠራውን ሥራ መገንዘብ የክርስትና ሕይወት በምልዓት እንዲገለጥ ያደርጋል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ያነሳሳናል፣ ያም ለክርስቶስ የመኖር ፍላጎትም ሆነ አቅም ከመንፈስ ቅዱስ እንደሚመጣ መገንዘብ የክርስትና ቁልፍ መረዳት*

*ነው፡፡ ይህም የእግዚአብሔርን ቃል አብርሆት በመስጠት መንፈስ ቅዱስ ለእኛ የሠራልንን ሥራ የምንገነዘብበት የመረዳት ባለጠግነት ክፍል ነው፡፡ የእግዚአብሔር ነገር እንዲርበን የሚያደርገን፣ ወደ እግዚአብሔር እንድንናፍቅ የሚያደርገን፣ የእግዚአብሔርን ሰዎች እንድንወድድ እና በዚህም አነሳሽነት እግዚአብሔርን እንድናገለግል የሚያስችለን እርሱ ነው፡፡ ያም የሰውየውን ማንነት ደብዛውን የማጥፋትን ብርቱ ተጋድሎ ይጠይቃል፡፡ "ሁሉም ነገር በእኔ ትከሻ ላይ ነው ያለው፣ እግዚአብሔር ማድረግ የሚገባኝን ነግሮኛል፣ አሁን ማድረጉ የእኔ ድርሻ ነው፣ መታዘዝ የእኔ ፋንታ ነው" የሚለውን የሰውን አስተሳሰብ ደብዛውን የማጥፋትን ተጋድሎም ይጠይቃል፡፡ እርግጥ ነው፣ ሃላፊነት አለብን፡፡ እግዚአብሔር ለእኛ ሊታዘዝልን አይችልም፣ ግን እርሱ መሻትን፣ ኃይልንና መረዳትን እንደሚሰጠን ልናውቅ ይገባል፡፡ ሁሉም ግን ለእርሱ ክብር ነው፡፡ [ዶ/ር ዶናልድ ዊትኒ]*

ከሌሎቹ የስላሴ አካላት ሁሉ በበለጠ ሁኔታ፣ መንፈስ ቅዱስ ይቅርታን፣ ደስታን፣ መልካምነትን፣ ብርታትን፣ ሰላምንና በድነታችን የምናገኛቸውን በረከቶች ሁሉ መቀበላችንን እርግጠኛ እንድንሆን በማድረግ በሕይወታችን በብዙ የሚሠራ እርሱ ነው፡፡ ስለዚህ፣ እነዚህን ነገሮች ተትረፍርፈው ማግኘት የምንሻ ከሆነ፣ የሚያድነውን ጸጋውን ይሰጠን ዘንድ ወደ እርሱ መማጠን ይኖርብናል፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ ስለታማኝነቱና ስለ ምህረቱ መንፈሱን ልናከብር ይገባል፡፡ ለእኛ የሚሰጠን የድነት ጸጋ የእኛን ምስጋና፣ አድናቆት፣ አምልኮና ፍቅር ለመቀበል የተገባው ከመሆን በላይ ያደርገዋል፡፡

የመንፈስ ቅዱስን የመፍጠር፣ የመቀደስና የድነት ኃይል ተመልክተናል፣ አሁን ደግሞ የመገለጥ ሥራዎቹን እንመለከታለን፡፡

## መገለጥ (ራዕይ)

መንፈስ ቅዱስ በስላሴ አካላት ውስጥ በጥቅሉ የመገለጥ፣ የምስክርነትና የመረዳት ወኪል በመሆን ይታወቃል፡፡ ይህንንም በዮሐንስ ምዕራፍ 14 ቁጥር 26፤ 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 2ከቁጥር 4 እስከ 10፤ ኤፌሶን ምዕራፍ 3 ቁጥር 5 እና በበርካታ ሌሎች ስፍራዎች እናነባለን፡፡ በመሠረቱ፣ በመንፈስና በመገለጥ መካከል ያለው ትስስር ግልጥ ነው ይህም እንደ ዮሐንስ ምዕራፍ 14 ቁጥር 17፣ ምዕራፍ 15 ቁጥር 26፣ ምዕራፍ 16 ቁጥር 13 ባሉት ክፍሎች መንፈስ ቅዱስ የእውነት መንፈስ ተብሎ በመጠራቱ ታይቷል፡፡ በ1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 6 እና 7 ላይ፣ ዮሐንስ ዘለቅ ብሎ እንዲህ ይላል፡

> በውኃና በደም የመጣ ይህ ነው እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ፤ በውኃውና በደሙ እንጂ በውኃው ብቻ አይደለም።

መንፈስም እውነት ነውና የሚመሰክረው መንፈስ ነው። (1ዮሐንስ 5፥6-7)

በተመሳሳይም መንገድ፣ ጳውሎስ በኤፌሶን ምዕራፍ 1 ቁጥር 17 ላይ እንዲህ ብሎ በመጥራት የመንፈሱን ሥራ አጠቃልሎታል፡

...የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ... (ኤፌ 1፥17)

ስለ መንፈሱ የመገለጥ ሥራ ሦስት ገፅታዎች እንነጋገራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ስለ አጠቃላይ መገለጥ እንነጋገራለን፡፡ ሁለተኛ፣ ስለ ልዩ መገለጥ እንነጋገራለን፡፡ ሦስተኛ፣ በአብርኾትና በውስጣዊ ምሪት ላይ እናተኩራለን፡፡ በመጀመሪያ አጠቃላይ መገለጥን እንመልከት፡፡

## አጠቃላይ መገለጥ

አጠቃላይ መገለጥ ማለት እግዚአብሔር የእርሱን ኑባሬ፣ ማንነት፣ ኀላዌ፣ ድርጊትና ፈቃድ ፍጥረተ-ዓለሙንና ሥራዎቹን በመጠቀም ለሰው ዘር በሙሉ እንዲታወቅ ያደረገበት ነው፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍት ስለዚህ አጠቃላይ መገለጥ በበርካታ ስፍራዎች ይናገራሉ፡፡ ለዋቤነት፣ በመዝሙር 8 ቁጥር 19፤ እና በሮሜ ምዕራፍ 1 እና 2፡፡ ለምሳሌ፣ ሮሜ ምዕራፍ 1 ቁጥር 20 ስለ አጠቃላይ መገለጥ በዚህ መንገድ ይናገራል፡

የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፤ ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ፤... (ሮሜ 1፥20)

ቅዱሳት መጻሕፍት በተደጋጋሚ አጠቃላይ መገለጥ መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር ኃይሉ በፍጥረ ውስጥ በሚያከናውናቸው ሥራዎች ይገለጣል ይላሉ፡፡ ይህም በፍጥረት በራሱ ውስጥ ደግሞም የተፈጠረውን በመጠበቅ ይገለጣል ማለት ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ሥራዎች ከመንፈስ ፈቃድና ባህርይ ውስጥ ይመነጫሉ፡፡ ስለዚህ የእርሱን ክንድ በእነርሱ ውስጥ ስንመለከት፣ ስለ እርሱ ማንነትና መሻት ያስተምሩናል፡፡

*በአጠቃላይ መገለጥ ሥራ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ እጅግ ወሳኝና አስፈላጊ ነው ምክንያቱም፣ እርሱ በመሠረቱ የፍጥረት ወኪል ነውና፡፡ እስከ አሁን ድረስ የእግዚአብሔርን ሕግ፣ እኛ አንዳንድ ጊዜ "የፍጥረት ሕግ" የምንለውን ጠብቆ የያዘ እርሱ ነው፡፡ ይህም ያለ አንዳች ልዩነት ለሁሉ የሚሰጠው መገለጥ ሲሆን፣ ይህ አንዳንድ ጊዜ*

*"ልዩ መገለጥ" ከምንለው የተለየ ማለትም በልባችን እርሱ ከሚሠራው ሥራ የተነሳ ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝና ጌታ መሆኑን ያወቅንበት ማለት ነው፡፡ አጠቃላይ መገለጥ ግን ለእግዚአብሔር ፍጥረታት ሁሉ የተሰጠ ነገር ነው፡፡ [ዶ/ር ሳይመን ቫይበርት]*

*ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ በማለት እግዚአብሔር ይነግረናል፡፡ አይናችንን ወደየትኛውም ስፍራ ዘወር ስናደርግ የእግዚአብሔርን ኃይል፣ የጥበቡን፣ የመልካምነቱን መገለጫዎች በፍጥረታቱ ዙሪያ እንመለከታለን፡፡ መንፈስ ቅዱስም እነዚህን የእግዚአብሔር መገለጦች በመውሰድ እና ወደ እኛም ኃያል በሆነ መንገድ በሕይወታችን ይገልጣቸዋል፡፡ እንግዲያው እኛም ወደ ፈጣሪያችን ዘወር እንላለን፡፡ [ዶ/ር ኤሪክ ኬ. ቶኔስ]*

## ልዩ መገለጥ

ለዓለም አጠቃላይ የሆነውን መገለጥ ከመስጠት ባሻገር፣ መንፈስ ቅዱስ ልዩ መገለጥን ይሰጣል፣ ተቀዳሚዋም ቤተክርስቲያን ናት፡፡

ልዩ መገለጥ ማለት እግዚአብሔር ኑባሬውን፣ ማንቱን፣ ኅላዌውን፣ ድርጊቱንና ፈቃዱን እርሱ በቀጥታ ወይንም በመልእክተኞቹ አማካይነት  ለተወሰኑ የሰው ዘሮች እንዲታወቅ የሚያደርግበት መገለጥ ማለት ነው፡፡

መንፈስ ቅዱስ ልዩ መገለጥን በቅዱሳት መጻሕፍት፣ በትንቢት፣ በህልም፣ በራዕይ፣ በመላእክት ጉብኝት እና በሌሎችም ባልተለመዱ መንገዶች ይሰጣል፡፡ ልዩ መገለጥ የሚሰጠው በተለይ የእግዚአብሔርን የድነት ስጦታ ለተቀበሉ ሰዎች ወይንም ቡድኖች ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን አብዛኛውን ጊዜ ልዩ መገለጥ የሚሰጠው ለአብርሃምና ለዘሩ ነበር፡፡ በአዲስ ኪዳን ደግሞ ለቤተክርስቲያን ተሰጥቷል፡፡ ልክ እንደ መንፈሳዊ ስጦታዎቹ ሁሉ፣ ልዩ መገለጥም እያንዳንዱን ሰው ለመለወጥና በእምነቱ እንዲያድግ ለማድረግ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ጥቅም ይሰጣል፡፡

መንፈስ ቅዱስ ከሰጠን ልዩ መገለጦች ሁሉ ትልቁ የኢየሱስ ክርስቶስ ትስጉት ነው፡፡ ዕብራውያን ምዕራፍ 1 ጌታችንን እንደ እግዚአብሔር የክብሩ መንፀባረቅ ያመሰግነዋል፡፡ አሁንም እንኳን፣ የክርስቶስን ንግግሮች ለትውልድ ሁሉ ሥልጣን በሰጣቸው ነቢያቱና ሐዋርያቱ አማካይነት በአብርሆተ ቅዱሳት መጻሕፍት፣ ወደ ክርስቶስ መምራቱን ቀጥሏል፡፡

የቅዱሳት መጻሕፍት ደራሲ መንፈስ ቅዱስ መሆኑ በማቴዎስ ምዕራፍ 22 ቁጥር 43፤ በማርቆስ ምዕራፍ 12 ቁጥር 36፤ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1 ቁጥር 16 እና ምዕራፍ 4 ቁጥር 25 እና

በ2ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ3 ከቁር 16 እስከ 17 ላይ ተጠቅሷል፡፡ ለምሳሌ ያህል፣ ጴጥሮስ በ2ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 20 እና 21 ላይ የጻፈውን አንብቡ፡

> ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ። (2ጴጥ 1፥20-21)

ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ፣ መንፈስ አዲስ መጽሐፍ አልገለጠም፡፡ ነገር ግን በብሉይም ሆነ በአዲስ በየዘመናቱ ለክርስቲያኖች ፍቃዱን ያስታውቅ ዘንድ የሚገልጣቸው ልዩ መገለጦች አሁንም ቀጥለዋል፡፡

ሦስተኛ፣ አጠቃላይ እና ልዩ መገለጥን ከመስጠት ባሻገር፣ በአብርሆትና ለእያንዳንዱ ሰው በሚሰጠው ውስጣዊ ምሪትም መንፈስ ቅዱስ ይሠራል፡፡

# አብርሆትና ውስጣዊ ምሪት

> *በ2ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 21 የብሉይ ኪዳን ነቢያት በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ከእግዚአብሔር የሆነውን እንደተናገሩ፣ ያም የሚያመለክተው መንፈስ ቅዱስ፣ ለነቢያት የሰጣቸውን መገለጥ እንድንረዳና እንዲያበራልን ለቤተክርስቲያን መሰጠቱን ነው፡፡ አዲስ መገለጥ የለም፣ ሆኖም የተገለጠውን ራሱን ለመረዳት በእግዚአብሔር መንፈስ አብርኖትን ልናገኝና ኃይልን ልንቀበል ይገባናል፡፡ [ዶ/ር ኖክስ ቻምብሊን]*

አብርኖት በአዕምሮአችን ውስጥ የነበረውን ቀደምት እውቀት እንድንረዳ ወይም እንድናውቅ የሚያደርገን መለኮታዊ ስጦታ ሲሆን፣ ይህም ልክ ጴጥሮስ በማቴዎስ 16 ቁጥር 17 ላይ ኢየሱስ መሲህ መሆኑ እንደተገለጠለት ዓይነት ነው፡፡

ውስጣዊ ምሪት ደግሞ አስቀድሞ ስሜታዊ ወይንም ደመ-ነፍሳዊ የነበረውን እውቀት የምንረዳበት ወይም የምንገነዘብበት የመለኮት ስጦታ ነው፡፡ ይህም ህሊናችንን እና እግዚአብሔር አንድን ተግባር እንድናከናውን የሚፈልግብንን ነገር የሚያካትት ነው፡፡

አብርኖትና ውስጣዊ ምሪት ዘወትር በግልፅነት አንዳቸው ከሌላቸው ተለይተው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አናገኛቸውም፡፡ ሁለቱም በእኩል ተግባራዊ በሚሆኑበት መንገድ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በተደጋጋሚ እናገኛቸዋለን፡፡ ይህንንም 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 9 እስከ 16፤ ኤፌሶን ምዕራፍ 1 ቁጥር 17፤ ቆላስያስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 9 እና 1ዮሐንስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 27 ላይ እናገኛለን፡፡ ለምሳሌ በኤፌሶን ምዕራፍ 1 ቁጥር 17፣ ጳውሎስ በዚህ መንገድ ይናገራል፡

የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ። (ኤፌ 1፥17)

በዚህ ስፍራ፣ ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስን "የጥበብና የመገለጥ መንፈስ" በማለት ይጠራዋል፡፡ አብርኖትንና ውስጣዊ ምሪትን በየፈርጅ ከማስቀመጥ አንፃር፣ ጥበብን እንደ ውስጣዊ ምሪት እና ራዕይን ደግሞ እንደ አብርኖት ለማየት እንፈተናለን፡፡ ጳውሎስም በልቡናው የያዘው ይኸው ይመስላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ያለምንም ግልፅ የሆነ ልዩነት ሁለቱንም የመንፈሱን ሥራዎች ለማመልከትም አስቦ ሊሆን ይችላል፡፡

*እኛ፣ ሁላችን፣ ያለ እርሱ መንፈሳዊ ዐይነ-ስውራን ነንና የመንፈስ ቅዱስ አብርኖት ያስፈልገናል፡፡ የሌሊት ወፎች በአካል ዕውር እንደሆኑ ሁሉ እኛም በመንፈስ የታወርን ነን፡፡ ማለቴ፣ ፀሐይን ማየት አይችሉም፡፡ ስለዚህም፣ ፀሐይ ስታበራ፣ በቀን በሚሸሸጉበት ዋሻ ጣሪያ ላይ ተለጥፈው ይውላሉ፡፡ ማየት የሚችሉት በጨለማ ሲወጡ ብቻ ነው፡፡ እኛም እንደ ሌሊት ወፍ በቀን የማናይ ነበርን፡፡ የእግዚአብሔር ብርሃን ያበራል፣ ኃጢአት ግን መንፈሳዊ አካላቶቻችንን ስላመሳቀላቸው፣ የእግዚአብሔርንና የቃሉን እውነታ ልንረዳ አልቻልንም፡፡ እግዚአብሔር በሆነ ስፍራ አለ የሚል ጭጋጋማ መረዳት ሊኖረን ይችል ይሆናል ግን የቅዱሳት መጻሕፍት ትዕዛዛት ለእኛ መሆናቸውን በማሰብ ተስፋዎቹም ለእኛ መሆናቸውን በማሰብ አናደንቃቸውም፡፡ የጌታ የኢየሱስ በቅዱሳት መጻሕፍት መገለጥ በእርሱ ወደምንታመንበትና ወደ አዲስ ሕይወት ወደምንገባበት መገለጥ ሊያስገባን በፊታችን ተዘርግቷል፡፡ አዲስ ኪዳን ይህንን ሁኔታ፣ የታወርን ነበርን፣ ደንቆሮዎች ነበርን፣ ልባችን ደንዳና ነበር ስለዚህም የእግዚአብሔር ቃል ለእኛ ምንም ትርጉም አይሰጠንም ነበር በማለት በስዕላዊ መንገድ ያስቀምጥልናል፡፡ አዲስ ኪዳን ከዚያም እንዲህ ይላል 2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 4 "በጨለማ ብርሃን ይብራ ያለ እግዚአብሔር ነውና" ይህም በፍጥረት ጅማሬም ተከናውኗል ግን እንደገናም "በክርስቶስ ፊት የእግዚአብሔርን የክብሩን እውቀት ብርሃን እንዲሰጥ በልባችን ውስጥ የበራ" በማለት የመንፈስ አብርኖት የተሰጠን መሆኑን እና ያም አብርኖት ሲሰጠን ክርስቶስን በመንፈስ ማየት መቻላችንን፣ የእርሱን እውንነት መረዳታችንን፣ እኛን ወደ እርሱ እየጠራን መሆኑን መስማታችንን ያረጋግጥልናል፡፡ [ዶ/ር ጄ. አይ. ፓከር]*

አብርኖትና ውስጣዊ ምሪት መንፈስ ቅዱስ የእርሱን ሕዝብ ስለ ገለጠው ፈቃዱ የሚያስተምርባቸው መደበኛ መንገዶች ናቸው፡፡ ስለዚህም ከዚህ አገልግሎት በሕይወታችን ተጠቃሚ ለመሆን ሦስት ነገሮችን ማድረግ ይገባናል፡፡ በመጀመሪያ፣ ባነበብነው ወቅት መንፈስ ቅዱስ እንድንረዳው በማድረግ የሚያግዘን መሆኑን በመረዳት መጽሐፍ ቅዱስን

ለማንበብ ራሳችንን መስጠት ይገባናል፡፡ ሁለተኛ፣ መንፈስ ቅዱስ ምሪትን፣ ጥበብን፣መረዳትን እና ለመታዘዝ ፈቃደኝነትን እንዲሰጠን ዘወትር በመጠየቅ ልንጸልይ ይገባል፡፡ ሦስተኛ፣ መንፈሱ እንደሚያስተምረን እውነት የተቀደሰ ሕይወት ለመኖር መወሰን ይኖርብናል፡፡

# 5 ማጠቃለያ

በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ በዚህኛው ትምህርት ስር፣ ስለ ትምህርተ መንፈስ ቅዱስ ተመልክተናል፡፡ የመንፈስን መለኮትነት በሃይማኖት መግለጫውና በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቱ ላይ ተመልክተናል፡፡ ባሕርያቶቹንና ከአብና ከወልድ ጋር ያለውን ግንኙነት መሠረት አድርገን ስብዕናውን ዳስሰናል፡፡ ስለ እርሱም የመፍጠር፣ የቅድስና፣ የጸጋና የድነት ኃይል ተነጋግረናል፡፡

ትምህርተ መንፈስ ቅዱስ ለክርስቲያኖች የማይነጥፍ ምንጭ ነው፡፡ በዘመናት ሁሉ ከሁሉ ስለሚቀርበን የረድኤታችን ምንጭ ስለ መንፈስ ቅዱስ ያስተምረናል፡፡ እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ ሕይወት መኖር የምንችልበትን ኃይል ሊሰጠን ሊያነቃቃን ወደሚችለው ወደ ስላሴ ሦስተኛ አካል ያመለክተናል፡፡ እምነታቸውን በእርሱ ላይ ስላደረጉ ሰዎች ጥቅም ዘወትር በሥራ ላይ መሆኑንና በዓለም ሁሉ ላይ እጅግ በጥልቀትና እያንዳንዱን በሚነካ መንገድ እግዚአብሔር የሚገባ መሆኑን በማሳየት ታላቅ መተማመንን ይፈጥርብናል፡፡